ወርኃዊ ጥንቅር፣ ቁ. 004
ሰኔ 2017 ዓ.ም.



# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ክራሞት

## እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

research@bridge-et.org

BRIDGE Research & Innovation-
Parliaments. Peace. Policy

## መልክዓ-ብሪጅ

መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ የጥናትና ምርምር ተቋም ነው። ብሪጅ፣ በዋናነት በኢትዮጵያ እና በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል አገራት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አሠተዳደር እንዲጎለብት እና ሰላም እንዲበለጽግ የሚሠራ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ፖሊሲ ተኮር የጥናት እና ምርምር ተቋም ነው።

## ተልዕኮ

ዲሞክራሲያዊ አሠተዳደር እና ሰላም ይጎለብት ዘንድ፣ ለፖሊሲ አወጣጥ ግብዓት የሚሆኑ፣ ተጨባጭነት ያላቸው ምርምሮችን ማድረግ እና የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ማቅረብ፤

## ርዕይ

በሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች እና በቀጠናዊ የሰላም፣ ዲሞክራሲያዊ አሠተዳደር እና ሰዋዊ እና ቁሳዊ ልማት ላይ፣ በኢጋድ ቀጠና ተቀዳሚ የምርምር እና ፖሊሲ አመንጪ ማዕከል መሆን፤

## መሠረታዊ ዕሴቶች

- አጽንዖተ ትኩረት፦ ከፍተኛ ትኩረት የተሰሩ እና ተጨባጭነት ያላቸው ጥናት ምርምሮችን ማቅረብ።።
- አዲስነት፦ ለዲሞክራሲያዊ አሠተዳደር እና ሰላም ተግዳሮቶች ፈጠራዊ እና ተለዋዋጭ መፍትሔዎች የታከለባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ማዋጣት
- ታማኝነት፦ ተዓማኒነት ያላቸውን የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ ተዓማኒነትን መጠበቅ

## ግቦች

ኢትዮጵያ እና በኢጋድ ቀጠና የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል ፓርላማዎች በሚከተሉት መንገዶች ማጠናከር

- ተጨባጭ ምርምሮችን መከወን
- የእንደራሴዎችን ብቃት ለማሳደግ የዐቅም ግንባታ ድጋፎችን ማድረግ
- ተጠያቂነትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ክንውኖችን መከታተል

+251 911 86 12 34
+251 115 57 74 96
research@bridge-et.org
https://bridge-et.org/
150096, Addis Ababa, Ethiopia.
Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.










# ማውጫ


በወሩ የተካሄደ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ ........ 1

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማ ........ 2

የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት ........ 6

የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር ........ 11

የፓርላማው ዲፕሎማሲ ........ 17

እንደራሴዎቹ ስለ'ራሳቸው በ'ራሳቸው ........ 18

ኢትዮጵያ ምን ተስማማች? ........ 19

ሹመት ........ 20

የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታ ........ 21

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ በወርኃ ሰኔ የተለያዩ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነቶቹን ከውኗል። ከእነዚኽ ዋንኛ ኃላፊነቶቹ መካከልም፣ ሕግጋት ማውጣት፣ የሥራ አሥፈፃሚ ተቋማት ሪፖርቶችን ማድመጥ፣ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ፣ የፌደራል ተቋማትን መጎብኘት እና የ2018 ዓ.ም. በጀት ማጽደቁ የሚጠቀሱት የወሩ የምክር ቤቱ አበይት ክንውኖች ናቸው። ከዚኽ በተጨማሪም፣ የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ወደ አዳራሹ መተው በተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ጥያቄዎች ላይ ማብራሪያ ሰተዋል። ይኽች የብሪፎ አራተኛ ዕትምም፣ እነዚኽን የምክር ቤቱን የሰኔ ክራሞት ጨምሮ፣ በወሩ ያጸደቀውን የቀጣዩን ዓመት በጀት ዝርዝር ነጥቦች ከብሪፎ አጭር ዳሰሳ ጋር አዳብላ እና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያዎች መካከል ዋንኞቹን ነጥቦች አጠናክራ እንዲህ ቀርባለች።

# በወሩ የተካሄዱ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባዎች

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን

**ሰኔ 3**

## 35ኛው መደበኛ ስብሰባ

**አጀንዳ**

በፌዴራል መንግስት የ2018 በጀት ዓመት ረቂቅ በጀት ላይ መወያየት እና ለዝርዝር ዕይታ ለበጀት፣ ፕላን እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መምራት፤

**ሰኔ 05**

## 36ኛው መደበኛ ስብሰባ

**አጀንዳ**

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ አመራሮችን መሾም፤

**ሰኔ 10**

## 37ኛው መደበኛ ስብሰባ

**አጀንዳ**

በወንጀል የተገኘ ንብረት ሕጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የቀረበውን ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጅን ማፅደቅ፤

**ሰኔ 12**

## 38ኛው መደበኛ ስብሰባ

**አጀንዳ**

የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የ 2017 በጀትዓመት የ11 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ማድመጥ እና በቀጣይ ትኩረት በሚያስፈልጋቸውጉዳዮች ላይ ግብረ መልስ ማቅረብ፤

**ሰኔ 17**

## 39ኛው መደበኛ ስብሰባ

**አጀንዳ**

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የመንግስት መሥሪያ ቤቶች 2016 በጀት ዓመት የሒሳብ የፋይናሽያል ሕጋዊነት እና የክዋኔ ኦዲት ሪፖርትን መገምገም እና መወያየት፤

**ሰኔ 19**

## 40ኛው መደበኛ ስብሰባ

**አጀንዳ**

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የ 2017 በጀት ዓመት የ11 ወራት የዕቅድ አፈፃጸም ሪፖርትን ማዳመጥ እና መገምገም፤

**ሰኔ 24**

## 41ኛው መደበኛ ስብሰባ

**አጀንዳ**

በፌዴራል መንግስት የ2018 በጀት ዓመት ረቂቅ በጀት ላይ መወያየት፤

**ሰኔ 26**

## 42ኛው መደበኛ ስብሰባ

**አጀንዳ**

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ የመንግስትን የ2017 የዕቅድ አፈጻጸም አስመልክቶ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ይሰጣሉ::

# ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማ

ባሳለፍነው ሰኔ ወር አጋማሽ ላይ ወደ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብቅ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ፣ ከእንደራሴዎቹ ለተነሱላቸው የበዙ ጥያቄዎች አኹናዊ የመንግሥታቸውን አቋም በስፋት አብራርተው ምላሽ ሰጥተዋል። ከአገር ቤት ፖለቲካ እስከ ኤርትራ፣ ከዐብይ ኢኮኖሚው እስከ ገዳማት ላይ እስከሚሰነዘር ጥቃት ድረስ ያሉ ጥያቄዎችን ያነሱት እንደራሴዎቹም፣ ሰዐታት የፈጀውን የጠቅላዩን ሰፊ ማብራሪያ አድምጠዋል።



ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ.ር. ዐብይ አህመድ

## “ችግሩ የስንፍና ፖለቲካ ነው”

ሰኔ 26 ላይ 42ኛ መደበኛ ስብሰባውን ያደረገው የኢትዮጵያ የእንደራሴዎች ምክር ቤት፣ ለጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ የተለያዩ ጥያቄዎችን አንስቷል። በቀዳሚነት እንደራሴዎቹ ያነሷቸው ጥያቄዎች፣ በአኹናዊው የአገሪቱ ሰላም እና ጸጥታ ዙሪያ የሚሽከረከሩ ነበሩ። ከፖለቲካ ተኮሮቹ ጥያቄዎች ሐሳባዊ ምላሽ መስጠት የጀመሩት ጠቅላዩ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የሰላም እና የፀጥታ ችግር ዋነኛው መንስኤ፣ የተሳሳተ የፖለቲካ አመለካከት መሆኑን አበክረው ሲናገሩ ተደምጠዋል። የስንፍና ፖለቲካ በአገራችን መንሰራፋት፣ በኃይል የታገዘ ፖለቲካ ማራመድ፣ ድህነት እና ሥራ አጥነት እንዲሁም ኋላቀርነት እና ዘረኝነት በአገራችን ዘላቂ ሰላምና ጸጥታ እንዳይፈጠር አባባሽ ችግሮች ስለመሆናቸው አስረድተዋል፡፡ የስንፍና ፖለቲካ ግጭት፣ ፀብ እና ተቃርኖን ይወልዳል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ የአሁኖቹን ፖለቲከኞች እንደ ድሮ ዘመን መሳፍንቶች እና መኳንንቶች ሳትሠራ አትብላ የሚለውን መርህ የማይቀበሉ እና ገበሬው ያረሰውን እንደሚካፈሉት መኳንንቶች ናቸው ሲሉም ገልጸዋቸዋል። አውርቶ አደር ፖለቲከኞች ዋና ሥራቸው አባልተው መብላት ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ካላጋጩ እና ካላባሉ ስለማይበሉ ግጭት በመፍጠር ጎፈንድ ሚ አልያም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ደመወዝ ይሰበስባሉ ሲሉም ተደምጠዋል። እነዚህ አሳቤዎች የውጭ ጣልቃ ገብነት ታክሎበት የባንዳነት ስሪት ደግሞ በመስፋቱ ችግሩን አባብሶታል፤ ኢትዮጵያ ስትጋጭ ትርፍ እናገኛለን ብለው የሚያስቡ እሳት ጫሪ ጭልፊቶች አሉ፤ ኢትዮጵያውያንም እሳት ጫሪዎችን ማወቅ እና ማረም ያስፈልጋል ሲሉም የአገሪቷ መሠረታዊ ፖለቲካዊ ችግር መነሾ ያሉትን ነጥብ ዘርዝረዋል።

ክላሽ ካነገትኩ ፍላጎቴ ይሳካል ብለው የሚያምኑ፣ አልፎም በሕዝብ የተመረጠን መንግስት በኃይል እና በወሬ እናፈርሳለን ብለው የሚያምኑት ቡድኖች ፍላጎት እንደማይሳካም ተናግረዋል፡፡ እነዚህ ኀይሎች ኀይልን በበላይነት መጠቀም የሚችለው መንግሥት መሆኑን የማይቀበሉ እንደሆኑ አስረድተው፣ የፖለቲካ ሐሳብን በምርጫ እንጂ በጠመንጃ ማሳካት አይቻልም ሲሉም ተሰምተዋል። በትጥቅ ትግል እንቅስቃሴ ውስጥ ያሉ ኀይሎች የሰላም አማራጭን ቀዳሚ ሊያደርጉ እንደሚገባ ያሳሰቡት ዐቢይ፣ እነዚህን ኀይሎች ማኅበረሰቡ በቃችሁ ሊላቸው ይገባል ብለዋል። መንግስት የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ለአፍራሽ ኀይሎች ምቹ እድልን የሚፈጥረውን ድህነት እና ኋላቀርነት ለመቅረፍ በትኩረት እየሰራ ነውም ብለዋል።

ዶ.ር. ዐቢይ አክለውም፣ ማኅበረሰቡ ሳይሸሽግ የታጠቁ አካላትን አትግደሉልኝ፤ እናንተም አትሙቱልኝ ማለት አለበት ሲሉ ገልጸው፤ ልጆቼን ፈተና እንዳይፈተኑ እና እንዳይማሩ አትከልክሉ፤ እንዳንሰራ አታድርጉ፤ ማዳበሪያ እንዳይመጣም አታድርጉ ማለት ይገባዋል ሲሉ እንደራሴዎቹ ላነሱት ሰላም ተኮር ጥያቄ ምላሽ ያሉትን ሰጥተዋል። በተመሳሳይም የፓለቲከኞች እና የጋዜጠኞችን እስር በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰው ጋዜጠኛ እና ፓለቲከኛ ስለሆነ ብቻ አይታሰርም ብለዋል። በእስር ላይ የሚገኙት ጉዳያቸው በፍርድ ቤት የተያዘ መሆኑን በማንሳት፣ ጥፋት የሌለባቸው አድርጎ ማሰቡ ነገ ችግር ይዞ ይመጣል ሲሉ፣ ለተነሳላቸው ጥያቄ የመንግስታቸውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ከዚኽ መሰሉ ጥቅል ፖለቲካ ተኮር ምላሻቸው ፈቅ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የትግራይን ጉዳይም በማብራሪያቸው ላይ አንስተው ነበር። በትግራይ ምድር አንድም ጥይት የመተኮስ ፍላጎት የለንም ያሉት የኢፌድሪ ጠቅላይ ጦር አዛዡ፣ በእኛ በኩል የማልማት ፍላጎት ነው ያለን ሲሉ ተናግረዋል፡፡ በትግራይ ክልል ቴሌኮም፣ ባንክ፣ መብራት እና ፋብሪካዎች ሥራ መጀመራቸውን እና መንግስት መቋቋሙን ያስታወሱት ዶ.ር. ዐቢይ፣ ተፈናቃይን በሚመለከት ራያ መቶ በመቶ መመለሳቸውን ገልጸው፤ ወልቃይት ያሉ ተፈናቃዮችን ለመመለስ እየተሰራ መሆኑ ለእንደራሴዎቹ ነግረዋቸዋል። ትግራይ ሳትቀየር ኢትዮጵያ ትቀየራለች የሚል እምነት የለንም ሲሉ የተደመጡት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የፌደራል መንግሥት ትግራይ ውስጥ ያለውን ችግር በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለው አስታውቀዋል፡፡ የትግራይ ሕዝብ መቶ በመቶ ጦርነት እንደማይፈልግ ያነሱት ርዕሰ-መንግሥቱ፣ ትግራይ የሚያስፈልገው ሰላም እና ችግሮችን በውይይት መፍታት ነው ብለዋል፡፡ የሃይማኖት አባቶች፣ ምሁራን እና ሁሉም ባለድርሻ አካላት ትግራይ ዳግም ወደግጭት እንዳትገባ መሥራት አለባችሁ ሲሉም አስገንዝበዋል፡፡

## የኢኮኖሚው ኹኔታ

ሰኔ 26 ዕለተ ኀሙስ በአንደራሴዎቹ ምክር ቤት የተገኙት የአገሪቷ ርዕሰ-መንግሥት፣ በዚያ ቀን ውሏቸው የአገሪቷን ፖለቲካ ብቻም ሳይሆን፣ መሠረታዊዉን የኢኮኖሚ አኹናዊ ኹኔታም ቁጥሮችን አስደግፈው በስፋት አብራርተዋል። ኢኮኖሚ ተኮር ማብራሪያቸውን፣ ስለ ኢትዮጵያ ማንሰራራት ዕሳቤ በማብራራት የጀመሩት ዐቢይ፣ ማንሰራራት የተባለው የለውጥ መትከል፣ መሰረት ማስያዝ ምዕራፍ ተጠናቆ ማሻሻያው ምርት የሚያሳይበት ጊዜ መድረሱን ለማመላከት መሆኑን ገልጸዋል። በመሆኑም በበጀት ዓመቱ አመርቂ፣ አስደናቂ እና በኢትዮጵያ ታይተው የማያውቁ ኢኮኖሚያዊ ድሎች የተመዘገቡበት ዘመን ነው ሲሉም ተናግረዋል። 'ርሳቸው የሚመሩት መንግሥት፣ ከዓመት ወደ ዐብይ-ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያው ለመግባት ምክንያት የሆኑት አራት የዐብይ-የኢኮኖሚ ስብራቶች መሆናቸውን ያስታወሱት ጠቅላዩ፣ አሁን ላይ ዓለም ላይ ባለው የዋጋ ግሽበት፣ ወረርሽኝ እና የንግድ ሥርዓቱ በዋዝቀበት፣ እንዲሁም የዓለም መንግሥታትን ትኩረት የሚስቡ በርካታ ጉዳዮች በበዙበት ጊዜ፣ ኢትዮጵያ ሰፋፊ ዓለም ዓቀፍ እና አገራዊ ችግሮች ቢኖሩባትም 8.1 በመቶ እድገት አሳይታለች ብለዋል፡፡ እነዚህ ድሎች ግብርናን ጨምሮ በተለያዩ የኢኮኖሚ ክፍሎች የተገኙ መሆናቸውን ለእንደራሴዎቹ ያስታወሱት ዶ.ር. ዐቢይ፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማረጋገጥ ብዝኃ የኢኮኖሚ ዘርፎችን መከተል እንደሚያስፈልግ አውስተዋል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዋልታ በሆነው የግብርና ዘርፍ በበጀት አመቱ 6.1 በመቶ ዕድገት ማስመዝገቡን የጠቀሱት ጠቅላዩ፣ የግብርና ዘርፍ ትኩረት የተሰጠው ለዕድገቱ ብቻ ሣይሆን በምግብ ራስን በመቻል፣ ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷን እንድታረጋግጥ የሚያስችላት ነው ብለዋል፡፡ በዚህ ረገድ ግብርና ከፍተኛ ሚና መጫወቱን የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ባለፉት ዓመታት 27 ሚሊየን የነበረው የሴፍቲኔት ተጠቃሚ ዜጎች ቁጥር፣ በተሰራው የውጤታማ የግብርና ሥራ የተነሳ 23 ሚሊየን የሚጠጉ የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች ራሳቸውን እንዲችሉ መደረጉን በማሳያነት አንስተዋል፤ ቀሪ 4 ሚሊየን ተረጂዎችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ነጻ ማውጣት እንደሚገባም ጨምረው አሳስበዋል፡፡ ከዚኽ ባለፈም፣ በበጀት ዓመቱ 3.5 ሚሊየን ሄክታር መሬት መታረሱን ብቻም ሳይሆን፣ ዘንድሮ 1.5 ቢሊየን ኩንታል በማምረት ከአምናው 24.7 በመቶ እድገት መመዝገቡን አብራርተዋል፡፡ በኢንዱስትሪው ንዑስ ክፍለ ኢኮኖሚ 12.8 በመቶ እድገት እንዲመጣ መታቀዱን እና በሲሚንቶ ምርት 6%፣ እንዲኹም በብረት ውጤቶች 18% እድገት መመዝገቡን በዚያ ቀን ላገኙቸው እንደራሴዎች አስረድተዋል። የማዕድን ዘርፉን በተመለከተም፣ በአፍሪካ ትልልቅ የማዕድን ሀብት ካላቸው አገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ መሆኗን ጠቁመው፤ ባለፈው አመት 4 ቶን ወርቅ ወደ ውጪ ሲላክ፣ ዘንድሮ ግን 37 ቶን ወደ ውጪ በመላክ 3.5 ቢሊየን ዶላር የውጭ ምንዛሬ መገኘቱን አብራርተዋል።

የአገልግሎት ዘርፉን በተመለከተም በቱሪዝም፣ ትራንስፓርት፣ በቴሌኮሙኑኬሽን እና በቴክኖሎጂ መስኮች በዚኹ በጀት አመት 8.1 በመቶ እድገት እንዲያመጣ መንግስታቸው ማቀዱን ተናገረዋል።

የኢትዮጵያን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚያፋጥኑ እና ኢኮኖሚውን በእጅጉ የሚቀይሩ አገራዊ ዕቅዶች በቅርቡ ተግባራዊ እንደሚደረጉ የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ ከዚኽ መካከልም የመጀመሪያው የጋዝ ምርት መሆኑን ተናግረዋል። የጋዝ ምርቱን ሲያወሱም፣ ከዚህ በፊት የነበሩ መንግሥታት ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም አለመሳካቱን እና ሥራውን የወሰዱ ኩባንያዎችም ውጤታማ ሳይሆኑ መቅረታቸውን አስታውሰዋል፡፡ አሁን ላይ ነባሮቹን ኩባንያዎች ያስወጣው መንግስታቸው፣ አቅም ያላቸውን ኩባንያዎች ወደሥራ በማስገባት አሁን ላይ ሥራው በመጠናቀቅ ላይ መሆኑን ተናግረዋል። ኢትዮጵያ ከመጪው መስከረም ወር ጀምሮ የጋዝ ምርቱን በማውጣት ወደ ውጪ እንደምትልክም ዐቢይ ሲናገሩ ተደምጠዋል። ከጋዝ ምርቱ በተጨማሪም፣ ለግብርናው ዘርፍ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው የሚታመንለትን የማዳበሪያ ፋብሪካንም፣ ከናይጄሪያው ባለሀብት አሊኮ ዳንጎቴ ጋር ለማቋቋም መንግስታቸው ስምምነት ላይ መድረሱን ጠበቅ አድርገው ሲናገሩ ተስተውለዋል። ይኸው ፋብሪካም፣ በቀጣዮቹ አርባ ወራት ውስጥ ተጠናቆ ወደ ሥራ እንደሚገባ ያነሱት ጠቅላዩ፣ መንግስት የኢንዱስትሪውን ንዑስ ክፍለ-ኢኮኖሚውን የበለጠ ለማጠናከር ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት አቅም ያላቸውን የውጪ ባለሀብቶች በመጋበዝ በቅርቡ የሶላር ፓኔል የሚያመርቱ ኩባንያዎች ገብተው ሥራ መጀመራቸውን እና በቅርቡም ወደ ምርት እንደሚገቡም አስረድተዋል፡፡

## “ኢትዮጵያ የጎረቤት አገራትን ሉዓላዊነት እንደምታከብረው ኹሉ የባሕር በር ጥያቄዋን ማክበር አለባቸው።”

የአገሪቷ ርዕሰ-መንግሥት እና የገዢው ፓርቲ ሊቀመንበር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፣ የዚኽ ዓመት የመጨረሻውን የእንደራሴዎች ምክር ቤት ውሏቸውን የዘጉት፣ በአገሪቷ ፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ላይ ማብራሪያ በመስጠት ብቻም ሳይሆን፣ የመንግስታቸውን አኹናዊ ዲፕሎማሲ እና ከኤርትራ ጋር ይፈጠራል በሚል ብዙዎች በሚሰጉበት ግጭት ዙሪያ ጭምር ነበር። ኢትዮጵያ ወደብ የማግኘት ሉዓላዊ መብት እንዳላት እና ይኽንን ለማሳካት በሰላማዊ መንገድ እንደምትቀጥል በድጋሚ የተናገሩት ዐቢይ፣ ኢትዮጵያ ያለጎረቤቶቿ ህልውና የላትም፤ ጎረቤቶቿም ያለ ኢትዮጵያ ህልውና የላቸውም ሲሉም ጠበቅ ያለ ንግግራቸውን አሰምተዋል። የባሕር በር ተደራሽነትን ማግኘት የምንፈልገው በኃይል ሳይሆን በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ላይ ተመስርተን ነው ሲሉ የተደመጡት ጠቅላዩ፣ ኹሉንም ነገር በሰላማዊ መንገድ ማሳካት እንፈልጋለን ሲሉ አበክረው ተናግረዋል። የጎረቤት አገራት ሉዓላዊነታቸውን እናከብራለን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ኢትዮጵያ ሉዓላዊ አገር ናት፤ ይህ ደግሞ የተሟላ እንዲሆን ጎረቤቶቻችን ኢትዮጵያ የባሕር በር ተደራሽነትን እንድታገኝ በአዎንታዊ መልኩ ምላሽ መስጠት አለባቸው ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተለይ ከኤርትራ ጋር ይፈጠር ይሆን ተብሎ የሚሰጋውን ጦርነት ያጣጣሉ ሲሆን፣ ከኤርትራ ጋር ጦርነት ይነሳል ለሚሉ አካላት፣ እኛ በበኩላችን ምንም ዓይነት ግጭት አንፈልግም፤ እነሱም እንዲሁ ማድረግ አለባቸው ሲል ምላሻቸውን ሰጥተዋል። ሆኖም ግን ኢትዮጵያ ራሷን የመከላከል አቅም እንዳላትም ጠቅሰው፣ ትኩረቷ ሰላም እና የጋራ ዕድገት ላይ መሆኑን አጽንኦት ሰጥተዋል። ባለፉት ሰባት ዓመታት ከጎረቤት አገሮች ጋር አንድም ግጭት አላጋጠመንም ሲሉም አክለዋል። የማገገም ጉዟችን እንዳይስተጓጎል ለማረጋገጥ ከኹሉም ጎረቤቶቻችን ጋር በሰላም መኖር እንፈልጋለን ሲሉ የተደመጡት ዐቢይ፣ ነገር ግን ሰላማችንን የሚያሰጋ ነገር ካለ ኢትዮጵያ ራሷን ለመከላከል በቂ አቅም አላት፤ ትልቅ ኢኮኖሚ፣ ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት እና ዘመናዊ ጦር ያላት አገር ናት ሲሉም አሳስበዋል። ኢትዮጵያ የጎረቤት አገራትን ሉዓላዊነት እንደምታከብረው ኹሉ የባሕር በር ጥያቄዋን ማክበር አለባቸው ያሉት ጠቅላይ ጦር አዛዡ፣ ኤርትራ ሉዓላዊ አገር ናት፤ በግድ የኢትዮጵያ አካል እንድትሆን አንፈልግም ሲሉ አጥብቀው ተናግረዋል። በኤርትራ በኩል ውጊያ እንደሚነሳ ሥጋት እንዳለ እንደሚወራ የገለፁት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በእኛ በኩል አንድም ጥይት አይተኮስም ብለዋል።

ከሁሉም ጎረቤት ሀገር ጋር ሰላማዊ ግንኙነት እንዳለ፣ ትብብር፣ ውይይት ብቻ እንደሚፈለግ እና ያንን ማስቀጠል የትኩረት አቅጣጫ ስለመሆኑም ጠቁመዋል። "በእኛ በኩል አንድ ጥይት አይተኮስም። በሰላም የማያኖር ጉዳይ ካለስ? ራሳችንን እንከላከላለን" ሲሉም አኹናዊ የመንግሥታቸውን የውጪ ጉዳይ አቋም ለእንደራሴዎቹ ነግረዋቸዋል።

በመጨረሻም፣ የሕዳሴ ግድብ አልቋል ሲሉ የተሰሙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ ክረምቱ ሲያልቅ እንደሚመረቅም ተናግረዋል። ግድቡ እንዳይመረቅ የሚያደርግ ነገር የለም ሲሉም፣ የታችኛው ተፋስስ አገራት በምርቃት ሥነ-ሥርዓቱ ላይ እንዲገኙ በዚኹ ንግግራቸው የአደባባይ ግብዣ አቅርበውላቸዋል።

# የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት

የተወካዮች ምክር ቤት፣ በጠቀስነው ሰኔ ወር ውስጥ አራት ሕግጋትን ሲያጸድቅ፣ አራት ረቂቅ ዐዋጆችን ደግሞ ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች ለዝርዝር ዕይታ ልኳል፤ ከዚኽ በተጨማሪም፣ በሦስት ረቂቅ ሕግጋት እና በ2018 ዓ.ም. በጀት ዙሪያ የውይይት እና የአስረጂ መድረክ አካሂዷል።

## የጸደቁ ሕግጋት

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በወርኃ ሰኔ ያጸደቀው ቀዳሚው ዐዋጅ፣ **በወንጀል የተገኘ ንብረትን ሕጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የቀረበውን ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጅ** ነበር። ሽብርተኝነትን እና ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል እና ከዓለም ዓቀፍ ሕጎች ጋር የተጣጣመ የተባለውን ይኽንኑ ዐዋጅ አስመልክቶ፣ የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ኢሳ ቦሩ ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳብ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የማሻሻያ ዐዋጁ፣ በወንጀል ተግባር የተገኘ ገንዘብን ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ድርጊትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በሚደረገው ዓለም ዓቀፍ ጥረት ላይ ኢትዮጵያ ያላትን ድርሻ በአግባቡ እንድትወጣ ሊያደርጋት የሚችል ነው ያሉት የተከበሩ ኢሳ፣ አመንጭ ወንጀሎችን በግልፅ ያስቀመጠ እና ለአፈፃፀም አስቸጋሪ እና ለትርጉም ተጋላጭ የነበሩትን ጉዳዮች ያስተካከለ ነው ሲሉም ተደምጠዋል። እንደራሴዎቹ በበኩላቸው፣ ረቂቅ ዐዋጁ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ ጋዜጠኞችን እና ነጋዴዎችን የሚጎዳ እንዳይሆን ሲሉ ስጋታቸውን ገልፀዋል፡፡ ለመሰሎቹ ጥያቄዎች ምላሽ እና ማብራሪያ የሰጡት የተከበሩ ኢሳ፣ ዐዋጁ ወንጀልን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የሚደግፍ ማንኛውንም ዜጋ እና ቡድን ተጠያቂ የሚያደርግ እንጂ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ ጋዜጠኞችን እና ነጋዴዎችን ብቻ በመየት ተጠያቂ አያደርግም ብለዋል። በመጨረሻም ይኽወ የተሻሻለው ዐዋጅ፣ ዐዋጅ ቁጥር 1387/2017 ሆኖ በሦስት ተቃውሞ እና በአንድ ድምፀ ተዐቅቦ በአብላጫ ድምፅ ጸድቋል፡፡

ያም ሆኖ ግና፣ በምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ልማድ ባልተስተዋለ መልኩ፣ ይኸው ዐዋጅ ከቀናት በኋላ ዳግም ማሻሻያ ተደርጎበት እንደገና ሊጸድቅ ችሏል። ለዚኽም መነሾ የሆነው፣ የዐዋጁ አንዳንድ ድንጋጌዎች ለሰብዓዊ መብት ጥሰት ክፍተት ይፈጥራል የሚሉ ድምጾች መሰማታቸውን ተከትሎ ነበር።

ዐዋጁ ከጸደቀ ከሃያ ቀናት በኋላ የተሰበሰበው ምክር ቤቱ፣ በምክር ቤቱ የአሠራር እና የአባላት ሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 አንቀፅ 49 (2)ሀ መሠረት፣ ውሳኔ የተሰጠበት ድንጋጌ እንዲታረም በሚል ከሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የቀረበውን የውሳኔ ሐሳብ መርምሮ አፅድቋል፡፡ ምክር ቤቱ በልዩ ስብሰባው፤ ከአሁን በፊት ውሳኔ የተሰጠበት ድንጋጌ እንዲታረም የቀረበለትን ዐዋጅ አርሞ አፅድቋል፡፡ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ኢሳ ቦሩም፣ ከአሁን በፊት የነበረው ዐዋጅ ድንጋጌ እንዲታረም መደረጉ አተገባበሩ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያስከትል ስለሚችል ዐዋጁን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ብለዋል። በዚህም፣ ከነባሩ ዐዋጅ አንቀፅ 26 ንዑስ አንቀፅ (3) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀፅ (4) ማሻሻያ የተደረገበት መሆኑን ሰብሳቢው አብራርተዋል፡፡

እንደራሴዎቹ በበኩላቸው፣ ዐዋጁ ለሰብአዊ መብት ጥሰት በር የሚከፍት በመሆኑ ድንጋጌውን መሻሻሉ ተገቢነት ያለው መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል፡፡ በፍትሕ ተቋማት በምርመራ ሂደት፣ በዜጎች ላይ አላስፈላጊ ድርጊት እንዳይፈፅሙ ክፍተት እንዳይሰጥ ለማስቻል የድንጋጌውን እርምት በጥሩ ጎን እንደሚረዱትም እንደራሴዎቹ ጠቅሰዋል። በምክር ቤቱ የአሠራር እና የአባላት ሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 አንቀፅ 49 (2)ሀ መሠረት ድንጋጌው ማሻሻያ ተደርጎበት፣ ውሳኔ ቁጥር 11/2017 ሆኖ በአንድ ድምጸ ተዐቅቦ፣ በአብላጫ ድምጽ ጸድቋል፡፡

እንደራሴዎቹ በዚኹ ወር በኹለተኝነት ያጸደቁት ዐዋጅ፣ የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት ረቂቅ ዐዋጅን ነበር። ረቂቅ ዐዋጁን አስመልክቶ የተዘጋጀውን የውሳኔ ሐሳብ ለእንደራሴዎቹ ያቀረቡት፣ በምክር ቤቱ የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ ነበሩ። ዐዋጁ፣ የውጭ አገር ሥራ ስምሪትን በተመለከተ ቀደም ሲል ሲሠራባቸው የነበሩት ዐዋጆች ክፍተቶች የነበሩባቸው በመሆኑ እና በጊዜ ሂደት ዐዋጆቹ ያላካተቷቸውን ጉዳዮችን በመለየት ዜጎች ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላል ያሉት ሰብሳቢው፣ ሕገ-ወጥ የውጪ አገር የሥራ ስምሪትን ለመከላከል እና በውጪ አገር ሥራ ስምሪት የዘመነ የአንድ ማዕከል የአሠራር ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚያስችልም ጠቁመዋል፡፡

የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ክብርት ሙፈሪያት ካሚል በበኩላቸው፣ ረቂቅ ዐዋጁ ዜጎች በሠለጠኑበት ሙያ ብቃታቸውን በቴክኖሎጂ በማረጋገጥ እና ከዚኽ ቀደም የነበሩ ተግዳሮቶችን በማስቀረት እንደ አገር ተወዳዳሪ እንድንሆን ያስችለናል ሲሉ ተደምጠዋል። ረቂቅ ዐዋጁ ዜጎችን ከሕገ-ወጥ ደላሎች የሚታደግ እና ሕገ-ወጥ የዜጎች ዝውውርን በማስቀረት ፋይዳው ከፍተኛ ስለመሆኑ የተናገሩት እንደራሴዎቹም፣ ዐዋጁን ቁጥር 1389/2017 አድርገው በሙሉ ድምጽ ይጸድቅ ዘንድ ፈቃዳቸው ሆኗል።

በዚኽ የብሪፉ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ወርኃ ሰኔ፣ እንደራሴዎቹ ያጸደቁት ሦስተኛው ዐዋጅ፣ **የውጭ አገር ዜጎች የመኖሪያ ቤት ባለቤት የሚሆኑበትን ደንብ አስመልክቶ የቀረበላቸውን ረቂቅ ዐዋጅ** ነበር። ለእንደራሴዎቹ ዐዋጁን አስመልክቶ የውሳኔ ሐሳብ ያቀረቡት የከተማ፣ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ፕሮፌሰር መሀመድ አብዶ፣ ዐዋጁ ኢትዮጵያ እያካሄደች ያለችውን ምጣኔ ሀብታዊ ለውጦችን የሚያሳልጥ እና የአገሪቱን የውጭ ዲፕሎማሲ ለማሻሻል የበኩሉን ሚና የሚጫወት ስለመሆኑ አብራርተዋል ተብሏል።

ዐዋጁ፣ የኢትዮጵያ ዜጎችን የመሬት ይዞታ የማግኘት መብት በማያጣብብ መልኩ የውጭ አገር ዜጎች የመኖሪያ ቤት ባለቤት የሚሆኑበት የሕግ ማዕቀፍ ነው ሲሉም ተሰምተዋል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ዶ.ር. እሸቱ ተመስገን በተራቸው፣ መሬት የመንግሥት እና የሕዝብ ሀብት በመሆኑ የውጭ አገር ዜጎች የመኖሪያ ቤት ባለቤትነት ፈቃድ የሚሰጥ ዐዋጅ እንጂ፣ በሪል ስቴት ዘርፍ እንዲሳተፉ የሚፈቅድ አይደለም ብለዋል። እሸቱ ለጥቀውም፣ ዐዋጁ የውጪ ምንዛሬ እጥረትን ለመቅርፍ፤ ለዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እና መዋዕለ-ንዋይን ለማሳለጥ ሚናው የጎላ እንደሚሆን ለእንደራሴዎቹ ነግረዋቸዋል።

በረቂቅ ዐዋጁ አስፈላጊነት ዙሪያ፣ የከተማ፣ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እና የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴዎች በጋራ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቂ ውይይት ማድረጋቸውንም የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል። ምክር ቤቱም፣ የውጭ አገር ዜጋ የመኖሪያ ቤት ባለቤትነት መብት ረቂቅ ዐዋጅ ሲል፣ ዐዋጅ ቁጥር 1388/2017 አድርጎ በአራት ድምጸ ተዐቅቦ እና በአብላጫ ድምጽ አፅድቋል፡፡

የእንደራሴዎቹ ሰኔ ወር የተጠናቀቀው፣ የቀጣዩን ዓመት በጀት በማጽደቅ ነበር። ምክር ቤቱ ባካሄደው በ42ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ የ2018 የፌዴራል መንግሥት በጀት 1 ነጥብ 93 ትሪሊዮን ብር አድርጎ በሙሉ ድምጽ አፅድቋል፡፡ በበጀቱ ዙሪያ የውሳኔ ሐሳብ ያቀረቡት የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ፣የዐብይ ኢኮኖሚው ግብ ለማሳካት በጀትን በቁጠባ እና በውጤታማነት ለመጠቀም ታሳቦ የተዘጋጀ ረቂቅ በጀት መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል። ሰብሳቢው አያይዘውም፣ ከጠቅላላው 1 ነጥብ 93 ትሪሊዮን ብር በጀት ውስጥ፣ ለመደበኛ በጀት የተመደበው 1.2 ትሪሊዮን ብር ሲሆን፤ ለካፒታል ደግሞ 415.2 ቢሊዮን ብር የተበጀተ መሆኑን ለእንደራሴዎቹ አስረድተዋል፡፡ የ2018 በጀት፣ ከባለፈው ዓመት በጀት ጋር ሲነፃፀር የ34.4 መቶ ዕድገት ማሳየቱን የጠቀሱት ሰብሳቢው፣ የበጀቱ አሸፋፈን በተመለከተም፣ ከአገር ውስጥ 1.1 ትሪሊዮን፣ ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች 129 ቢሊየን እና ከልማት አጋር ድርጅቶች 236 ቢሊዮን፣ እንዲሁም ከአገራዊ ዕቅዶች ዕርዳታ 47 ቢሊዮን ብር ለማግኘት እንደታቀደ ጠቅሰው፣ የአገር ውስጥ የውጭ ዕርዳታ ገቢ 81 በመቶ የሚሆነውን እንደሚሸፍንም ሰፋ አድርገው አብራርተዋል። በመጨረሻም፣ የፌደራል መንግሥት የ2018 ረቂቅ በጀት ዐዋጅ፣ ዐዋጅ ቁጥር 1390/2017 ሆኖ በሙሉ ድምጽ ፀድቋል፡፡ (በዚኹ የቀጣይ ዓመት በጀት ዙሪያ፣ ሰፋ ያሉ የበጀቱን ኢኮኖሚያዊ ነጥቦች ጨምሮ፣ አጠር ያለውን የብሪፉን ዳሰሳ በገጽ 21 ይመለከቷል)።

## ረቂቅ ሕግጋት




የረቂቅ አዋጆች ማብራሪያን የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ ባቀረቡበት ወቅት

በወርኃ ሰኔ፣ የኢትዮጵያ የእንደራሴዎች ምክር ቤት የተወያየበት ረቂቅ ዐዋጅ፣ **የዕፅዋት ጥበቃ እና ኳራንታይን የተሰኘውን ረቂቅ ዐዋጅ** ነበር። የረቂቁን ማብራሪያ ያቀረቡት፣ በምክር ቤቱ የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር የሆኑት የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ ነበሩ። ዐዋጁ የዘመናዊ የዕፅዋት ጥበቃ እና ኳራንታይንን ለማዘመን፣ መጤ እና ወራሪ ተባዮችን ለመከላከል፣ በዘርፉ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ፋይዳው ግዙፍ ነው ሲሉም ለምክር ቤቱ አብራርተዋል። ተቃዋሚው የምክር ቤት አባሉ የተከበሩ ዶ.ር. ደሳለኝ ጫኔ በበኩላቸው፣ ረቂቁ የሚመራለት ቋሚ ኮሚቴ ወራሪ ተክሎች በተለይም በተለምዶ እምቦጭ የተባለው መጤ ተክል እያደረሰ ያለውን ጉዳት ግምት ውስጥ አስገብቶ ሊሰራ እንደሚገባ አስገንዝበዋል ተብሏል። ረቂቅ ዐዋጁም ለዝርዝር ዕይታ ለምክር ቤቱ የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሙሉ ድምጽ ተመርቷል።

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በኹለተኛነት የተመለከተው፣ **የስታርትአፕ ረቂቅ ዐዋጅን** ሲሆን፣ ይኽንን ረቂቅ ዐዋጅን አስመልክቶም የተናገሩት ተስፋዬ በልጅጌ ነበሩ። ተጠሪ ሚኒስትሩም በማብራሪያቸው፣ ረቂቅ ዐዋጁ ኢኖቬሽን ነባር አሠራሮችን፣ የምርት እና የአገልግሎት ሂደቶችን እና ምርቶችን በሳይንሳዊ መንገድ በመቀየር ሰዎች ሕይወታቸውን በተሻለ መንገድ እንዲመሩ የሚያደርግ መሆኑን መግለፃቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ይጠቁማል። በኢትዮጵያ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂን ከማስረጽ እና በኢኮኖሚው ውስጥ ሊያመጣ የሚችለውን አዎንታዊ ውጤት ጨምሮ፣ በተለይም ለወጣቶች የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅሙም ከፍተኛ በመሆኑ፣ ይህን ታሳቢ በማድረግ የሕግ ማዕቀፍ ለመፍጠር አስፈላጊ መሆኑን ለዐዋጁ መዘጋጀት መነሾ መሆኑን ተስፋዬ አክለው ጠቅሰዋል። ምክር ቤቱም፣ ረቂቅ ዐዋጅን፣ ዐዋጅ ቁጥር 2320/2017 ሲል፣ ለዝርዝር ዕይታ ለሰው ሃብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሙሉ ድምጽ መርቶታል።

ሰኔ መገባደጃ ላይ 4ኛ ዓመት 2ኛ መደበኛ ስብሰባውን ያደረገው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሥተዳደር እና የምርጫ ሥነ-ምግባር ረቂቅ ዐዋጅንም ተመልክቶ ነበር። በረቂቅ ዐዋጁ ላይ ዙሪያ አጭር ማብራሪያ ያቀረቡት የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ ቀደም ሲል የነበረውን ዐዋጅ ተከትሎ ቦርዱ ያሥፈጸመው ጠቅላላ ምርጫ በሕግ ክፍተት ምክንያት የተስተዋሉ ችግሮችን፣ እንዲሁም በፖለቲካ ፓርቲ አሥተዳደር ስራዎች ላይ ያሉ የሕግ ክፍተቶችን ለማረም የተዘጋጀ የማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጅ መሆኑን መናገራቸው ተዘግቧል። የማሻሻያ ዐዋጁ የምርጫ ተሳታፊ ባለድርሻ አካላት ምርጫውን ሰላማዊ እና ፍትሓዊ በማድረግ ከማስፈጸም አንጻር ያላቸውን መብት እና ግዴታ ለመደንገግ የወጣ ስለመሆኑም ታገሰ ጠቁመዋል፡፡ ረቂቅ ዐዋጁ ወጥነት፣ ግልጽነት እና ከሕገ-መንግሥታዊ መርሆች እና ዓለም ዓቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎች ጋር በማጣጣም ነባሩን ሕግ በማሻሻል እንደሚያጠናክርም ገልጸዋል ተብሏል።

ማሻሻያው ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ሌሎች የተገለሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች በምርጫ እና በፖለቲካ የተሻለ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያስችላልም ተብሏል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ነጻነት እና የአሰራር ቅልጥፍና ለማሳደግ፣ ሰፊ የፖለቲካ ተሳትፎ እና ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚያስችል ማሻሻያ ዐዋጅ እንደሆነም አፈ-ጉባኤው ባቀረቡት ማብራሪያ ላይ ገልጸዋል፡ ፡ የምክር ቤቱ አባላት በበኩላቸው ረቂቅ ዐዋጁ የተመራለት ቋሚ ኮሚቴ በጥልቀት ሊያየው ይገባል ያሏቸውን ሐሳቦች አቅርበው፣ ረቂቅ ዐዋጅ ቁጥር 24/2017 በሚል ስያሜ፣ ለዝርዝር ዕይታ ለዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሙሉ ድምጽ መርተውታል።

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በወርኃ ሰኔ የተመለከተው አራተኛው ረቂቅ ዐዋጅ፣ **የገቢ ግብርን ለማሻሻል የቀረበለትን ረቂቅ ዐዋጅ** ነበር። ረቂቅ ዐዋጁን አስመልክቶ አጠር ያለ ማብራሪያ ያቀረቡት፣ በምክር ቤቱ የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታው የተከበሩ መሰረት ኃይሌ ነበሩ። በገቢ ግብር ዐዋጅ ላይ የተደረገው ማሻሻያ፣ የኢትዮጵያን የግብር ሥርዓት ዘመናዊ በማድረግ የግብር ፍትሓዊነትን ለማረጋገጥ፣ የግብር ሕግጋት እንዲከበሩ ለማድረግ እና የመንግስትን ገቢ ለማሳደግ የዐዋጁ መሻሻል አስፈላጊ እንደሆነም ሚኒስትር ዴኤታዋ ማብራራታቸውን ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል።

የገቢ ግብር ማሻሻያ ዐዋጁ ዋንኛ አላማዎች ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ ያለውን የግብር ጫና መቀነስ፣ የግብር መሠረትን ማስፋት እና ለአነስተኛ የንግድ እንቅስቃሴዎች ቀላል የግብር አከፋፈል ሥርዓት መዘርጋት መሆኑን የተናገሩት ሚኒስትሯ፣ የአገራችንን ኢኮኖሚያዊ ኹኔታዎች ከግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ የግብር ሥርዓቱን ከዓለም ዓቀፍ ልምድ ጋር ማጣጣም የሚያስችል ነው ሲሉም ተደምጠዋል። በመጨረሻም ምክር ቤቱ የቀረበውን ረቂቅ ዐዋጅ ቁጥር 25/2017 አድርጎ ለዝርዝር ዕይታ ለፕላን በጀትና ፋይናንስ ቋሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሙሉ ድምጽ መርቶታል።

## አስረጂ መድረኮች



የከተማ መሰረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ፕሮፌሰር መሀመድ አብዶ

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በወርኃ ሰኔ ካደረጋቸው የአስረጂ መድረኮች መካከል ቀዳሚው የነበረው፣ **የባሕር ማዶ ሰዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የቋሚ ንብረት ባለቤትነትን አስመልክቶ ባዘጋጀው ረቂቅ ዐዋጅ** ዙሪያ ነበር። በቀደመው ግንቦት ወር በዚኹ ዐዋጅ ዙሪያ የተካሄደውን አንድ የአስረጂ መድረክ ተከትሎ፣ በዚኹ ሰኔ ወርም በተለያዩ ቀናት፣ የተለያዩ የአስረጂ መድረኮች ተካሂደዋል። ቀደም ብሎ ሰኔ 9 ላይ የተካሄደውን የአስረጂ መድረክ ያዘጋጁት፣ የምክር ቤቱ የከተማ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች እና የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴዎች ነበሩ። የከተማ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ፕሮፌሰር መሀመድ አብዶ፣ በረቂቅ ዐዋጁ ላይ ጥሩ ውይይት መደረጉን ገልጸው፣ በዐዋጁ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ለውጭ ዜጎች ክፍት በመደረጉ የሚመጣ ብዙም ጉዳት እንደማይኖር የሌሎች አገሮች ልምድ ሲጠቅሱ ተሰምተዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. እሸቱ ተመስገን በበኩላቸው፣ ውይይቱ ቀደም ሲል የነበረውን ብዥታ ያጠራ መሆኑን አንስተው፣ ለመኖሪያ ቤት ግንባታ ያለውን የገንዘብ አቅርቦት ችግር ለመቅረፍ በረጅም ጊዜ እና በዝቅተኛ ወለድ የሚያበድር ባንክ እንዲኖር ቢደረግ የተሻለ መሆኑንም አክለው ተናግረዋል ተብሏል። የፍትሕ ሚኒስትሯ ሀና አርዓያ ሥላሴ ደግሞ፣ ዐዋጁ በሪል ስቴት ላይ የውጭ ዜጎች የቤት ባለቤት እንዳይሆኑ እና እንዳይሳተፉ ያለውን ለረጅም ጊዜ የቆየ ክልከላ በማንሳት ለዘርፉ እድገት ትልቅ አስተዋጾ ያደርጋል ብለዋል። የከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስትሯ ጫልቱ ሳኒ በበኩላቸው፣ ዐዋጁ በመኖሪያ ቤት አቅርቦት ላይ ያለውን ችግር በመፍታት የአገራዊ ለውጡ አንድ አካል እንደሚሆን መግለፃቸው ተጠቁሟል።

የምክር ቤቱ የከተማ መሠረተ ልማት እና የትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዚኹ ዐዋጅ ዙሪያ ከሦስት ቀናት በኋላም፣ ከተለያዩ ተቋማት ኃላፊዎች ጋር ውይይት አድርጎ ነበር። በውይይቱ ላይ ከተገኙ ተቋማት መካከልም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ የፌደራል ጠበቆች ማኅበር፣ የኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይገኙበታል። የውይይቱ ተሳታፊዎችም በረቂቅ ዐዋጁ ዙሪያ በርካታ ጥያቄዎችን እና አስተያየቶችን አንስተው ነበር። ከተነሱት መካከልም የቤት አልያም የመሬት ባለቤትነት ከሕገ-መንግሥቱ አኳያ ለዜጎች የተሰጠ መብት በመሆኑ ረቂቅ ዐዋጁ ከሕገ-መንግስቱ ድንጋጌ ጋር አይጣረስምን? የውጭ ዜጎች የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ገዝቶ በመሸጥ ሂደት ውስጥ ምን አይነት የሥራ ዕድል ይፈጥራል እና ሌሎችም ከሕግ እና ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አንፃር የቀረቡት ጥያቄዎች ተጠቃሽ ነበሩ።

የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሚለው አገላለጽ አኳያ የተለያዩ ጥያቄዎች የሚያስነሳ ነው ያሉት ሰብሳቢው፣ ብዥታን ለማጥራት ከምን አንፃር እንደተገለፀ አቅጣጫ መስጠት ወይም በቀጥታ የመኖሪያ ቤት በሚለው መተካት ያስፈልጋል ሲሉ አሳስበዋል። የቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ እሸቱ ተመስገን በበኩላቸው፣ የቀረበው ረቂቅ ዐዋጅ ከሕገ-መንግሥቱ ጋር ምንም አይነት ተቃርኖ እንደሌለበት አጥርቶ ማስቀመጥ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል ተብሏል። የውጭ ዜጎች የሚለውን አባባል በተመለከተ፣ ለሕዝብ ግልጽነትን ከመፍጠር አኳያ ትውልደ ኢትዮጵያውያንን የሚመለከት መሆኑን በረቂቅ ዐዋጁ በግልጽ ማመላከት እንደሚገባም አሳስበዋል።

በዚኹ መድረክ ላይ የተገኙት የከተማ መሰረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታዋ ሄለን ደበበም፣ ዐዋጁ ለዐብይ ኢኮኖሚው ማሻሻያ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው አንስተው፣ የዐዋጁን አስፈላጊነት በሚገባ ለማስጨበጥ ጥረት መደረጉን ማብራራታቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል። በዚኹ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ በማግስቱ በተዘጋጀ ሌላ የአስረጂ መድረክ የተገኙት ሄለን፣ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸው ዋነኛ ኃላፊነት፣ የከተማ መሬትን ማስተዳደር እንደሆነ በመጥቀስ፣ ነገር ግን ከገጠር መሬት ጋር ሊኖረው የሚችለውን ትስስር ከወዲሁ ታሳቢ በማድረግ ስትራቴጂዎችን ቀርፀው እየሰሩ መሆኑን ሲናገሩ ተደምጠዋል። የፍትሕ ሚኒስትሯ ሀና አርዓያ ሥላሴ እንዲሁ፣ ከዚህ በፊት በተደረጉ ተከታታይ መድረኮች አማካኝነት በረቂቅ ዐዋጁ ላይ የተሻለ ግልጽነት ላይ መደረሱን ገልጸው፣ የዐዋጁ ዋነኛ ዓላማ የውጭ አገር ዜጎች የቤት ባለቤት የሚሆኑበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር እንደሆነ ለመድረኩ ተሳታፊዎች አስታውሰዋቸዋል።

በዚኹ ሰኔ ወር ላይ የተካሄደው ኹለተኛው የአስረጂ መድረክ፣ **የውጭ አገር የስራ ስምሪት ዐዋጅን** አስመልክቶ የተደረገው ነበር። በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ በሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር በተዘጋጀው ይኸው መድረክ ላይ የተገኙት የቋሚው ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ፣ ረቂቅ ዐዋጁ የዜጎችን እና የአገርን ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ አሁን ያለውን የአገልግሎት አሰጣጥ በማሻሻል ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ግዙፍ ፋይዳ እንዳለው ተናግረዋል። የሥራ እና ክህሎት ሚኒስትሯ ክብርት ሙፈሪያት ካሚል በበኩላቸው፣ የረቂቅ ሕጉ መነሻ ግብ እና አላማ በውጭ አገር ለስራ የሚሰማሩ ኢትዮጵያውያን ዜጎች መብታቸው እና ክብራቸው በዘላቂነት መጠበቁን ለማረጋገጥ እንዲሁም አገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት ያለባትን ጥቅም ለማስጠበቅ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

በረቂቅ ዐዋጁ ወደ ውጭ አገራት ሰራተኞችን የሚልኩ ኤጀንሲዎች በሚያስዙት የዋስትና ገንዘብ መጠን ላይ ማሻሻያ የተደረገ ሲሆን፣ ከዚህ በፊት ትንሹ 100 ሺህ ዶላር ሲሆን፣ ይሄን ዝቅ በማድረግ ትንሹ የዋስትና የገንዘብ መጠን ወደ 50 ሺህ ዶላር ዝቅ እንዲል እና ከፍተኛው ደግሞ 250 ሺህ ዶላር እንዲሆን መደረጉንም ሚኒስትሯ ጠቁመዋል።

በዚኹ ረቂቅ ዐዋጅ ዙሪያ ይኸው ኮሚቴ ባደረገው ተጨማሪ ውይይት ላይ የተገኙት የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢዋ ክብርት ዶ.ር. ቤተልሔም ላቀው፣ ረቂቅ ዐዋጁ ለዜጎች መብት እና ጥቅም መከበር በርካታ አንኳር የሆኑ ሀሳቦችን ያካተተ መሆኑን በመጥቀስ፣ ከዚህ በፊት በዜጎች ላይ ይደርስ የነበሩትን ችግሮች ይፈታል ማለታቸው ተሰምቷል። ሚኒስትሯ ሙፈሪያት ካሚል በበኩላቸው፣ ረቂቅ ዐዋጁ ከአገራዊ የለውጥ አጀንዳ ተነጥሎ የሚታይ እንዳልሆነ ገልጸው፣ በተለይም ከውጭ አገር ሥራ ስምሪት አንፃር ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ ላይ የተመሰረተ እንዲሁም የዜጎችን ኹለንተናዊ ደህንነት በማስጠበቅ ዘርፉ እንዲዘምን እና የተሳለጠ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል እንዲሆን የሚያግዝ ነው ብለዋል ተብሏል።

የኢፌድሪ የእንደራሴዎች ምክር ቤት፣ በወርኃ ሰኔ አጋማሽ ያካሄደው ሌላይኛው አስረጂ መድረክ፣ ለቀጣዩ **2018 ዓ.ም. የቀረበውን በጀት** የተመለከተው ነበር። በዚኹ አስረጂ መድረክ ላይ የተገኙት የምክር ቤቱ የኘላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ፣ የቀረበው የ1.93 ትሪሊየን ብር በጀት ትልቅ መሆኑን ገልጸው፤ በጀትን ለታለመለት አላማ በቁጠባ መጠቀም እንደሚያስፈልግ በመድረኩ ላይ ገልጸዋል ተብሏል።

ከአጠቃላይ አገራዊ ኢኮኖሚው የተገለጸው የ1 በመቶ የበጀት ጉድለት፣ በፊት ከነበረው አንጻር ጥሩ ለውጥ ያለው መሆኑን የጠቆሙት ደሳለኝ፣ ከተቋማት የተነሱ ዘመናዊ ቴክኖጂን ለመጠቀም እና ለሕንጻዎች እድሳት የሚጠየቁ በጀቶች ከፍተኛ መሆናቸውን አንስተው፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት በመለየት በአግባቡ ሊሰራባቸው እንደሚገባ መናገራቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም አለማየሁ በበኩላቸው፣ በጀቱ የመንግስት የልማት ዕቅዶችን ሊያሳካ በሚችል ደረጃ በተለያየ መልኩ የሚነሱ የልማት እና የኑሮ ውድነት ጥያቄዎችን ሊፈታ በሚችል መልኩ መዘጋጀቱን ‘ርሳቸው በሚመሩት ቋሚ ኮሚቴ በኩል እንደሚታይ ገልጸዋልም ተብሏል። ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ የሰጡት የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታው ዶ.ር. እዮብ ተካልኝ፣ የበጀቱ ትኩረት በተረጋጋ ዐብይ ኢኮኖሚ ውስጥ ዘላቂ የሆነ ልማት ለማስቀጠል እና የፊሲካል እና የገንዘብ ፖሊሲው ተናቦ እንዲሄድ ለማድረግ መሆኑን ገልጸዋል። በጀቱ መንግስት የተረጋጋ ኢኮኖሚ እንዲኖር ለማድረግ ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ መሆኑን ያነሱት ዶ.ር. እዮብ፣ የተለያዩ ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በተቋማት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በመለየት ተጨማሪ በጀት ጥያቄ በማያስነሳ መልኩ ለማዘጋጀት ጥረት መደረጉን መናገራቸው ተሰምቷል፤ ከዚኽ ባለፈም፣ ተቋማት የተሰጣቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ስለማዋላቸው ክትትል እንደሚደረግም ተናግረዋል።

የወሩ የእንደራሴዎቹ የመጨረሻ አስረጂ መድረክ የነበረው፣ **በግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት እና አስተዳደር ረቂቅ ዐዋጅ** ዙሪያ፣ የምክር ቤቱ የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከግብርና ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት ከተወጣጡ የስራ ኃላፊዎች ጋር ያደረገው ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ሰሎሞን ላሌ፣ ረቂቅ ዐዋጁ ኢትዮጵያ የተያያዘችውን የግብርና ዘርፍ በማዘመን ምርት እና ምርታማነትን በማሳደግ በምግብ ሰብል ራሷን ለመቻል እና የውጭ ምንዛሪን በማሳደግ የአገሪቷን ብልጽግና ለማረጋገጥ ትልቅ አበርክቶ አለው ብለዋል ተብሏል።

ረቂቁ በሚጸድቅበት ወቅት የግብርናውን ዘርፍ ለማሳደግ በሚደረገው እንቅስቃሴ መንግስት ከሚያደርገው ተሳትፎ በተጨማሪ የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትን የሚያሳትፍ መሆኑን የጠቀሱት ሰሎሞን፣ ዘርፉ ደረጃቸውን የጠበቁ የተለያዩ እውቀት እና የቴክኖሎጂ አቅም ያላቸው አካላት እንዲሳተፉ የሚስችል ነው ብለዋል፡፡ የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታው ዶ.ር. መለሰ መኮንን በበኩላቸው፣ ዐዋጁ ያስፈለገበት ዋና አላማ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት እና አስተዳደር በግብርና ልማት እና በተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ ያለውን የተደራሽነት፣ የጥራት እንዲሁም የአፈጻጸም ውስንነት ለመቅረፍ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ነው ብለዋል ተብሏል፡፡ በመድረኩ ላይ በረቂቅ ዐዋጁ ዙሪያ የትርጉም ግልፀኝነት፣ በዐዋጁ መካተት እና መቀነስ በሚገባቸው ፍሬ ነገሮች እንዲሁም በረቂቅ ዐዋጁ አስፈላጊነት እና ጠቀሜታ ዙሪያ ከቋሚ ኮሚቴው አባላት እና በሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ጽሕፈት ቤት የሕግ ባለሙዎች የተለያዩ ጥያቄዎች ተነስተው፣ በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እና የሥራ ኃላፊዎች ሰፋ ያለ ማብራሪያ እና አስተያየት እንደተሰጠባቸው ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ያሳያል።

# የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር

የ ኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደራሴዎች፣ ከዋና ዋና ሥራዎቻቸው አንዱ የሆነው የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር ሲሆን፤ በዚኽ ረገድም፣ በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ወርኃ ሰኔ የተለያዩ የአሥፈጻሚ ተቋማትን ሪፖርቶች አድምጠዋል፤ ከምክር ቤቱ ወጣ ብለውም የተለያዩ ተቋማትን በ‘የኮሚቴዎቻቸው አማካኝነት በአካል ሲመለከቱ፣ በዛ ያሉ የመስክ ጉብኝቶችንም ከውነዋል።



የኢፌዴሪ መከላከያ ሚንስቴር ሚኒስትር ክብርት ኢንጂነር አይሻ መሐመድ፣ የኢፌዴሪ መከላከያ ስራዊት ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፣ ውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ነጎዎ እና ምክትል ሰብሳቢ ዶ.ር. ፈትሂ ማህዲ

## የተቋማት ሪፖርቶች

የተለያዩ የፌዴራሉ የመንግስት ተቋማት፣ ተጠሪ ለሆኑባቸው የተለያዩ የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች፣ ከዐሥር እስከ ዐሥራ አንድ ወራት የሚሸፍነውን የሥራ አፈፃፀማቸውን ሪፖርት በወርኃ ሰኔም ሲያቀርቡ፣ ምክር ቤቱም ከዚህ አለፍ ብሎ የፌደራል ተቋማትን የኦዲት ሪፖርቶች አድምጧል።

በወሩ መጀመሪያ፣ የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በማድረግ፣ ከምክር ቤቱ የመንግስት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጋር የተወያየው **የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን** ነበር። ቋሚ ኮሚቴው ከተቋሙ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ባደረገው ይኸው ውይይት፣ ተቋሙ ለኅብረተሰቡ ከሚሰጠው አገልግሎት አንፃር ሚናው ከፍተኛ በመሆኑ፣ ማኅበራት በሕግ ማዕቀፍ በመመራት ከብልሹ አሰራር እንዲውጡ ለማረም እየተሰራ ያለው ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት የቋሚ ኮሚቴው አባላት አስገንዝበዋል ተብሏል። አባላቱ አክለውም፣ በኹሉም ማኅበራት ላይ አስፈላጊውን ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ ለማኅበረሰቡ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ እንደሚቻልም የኮሚቴው አባላት አመላክተዋል፡፡ ስረድተውል፡፡

የግብይት ሥርዓቱን ለማዘመንም፣ መመሪያ በማዘጋጀት የገበያ የፋይናንስ አቅምን ማጠናከር ይገባልም ብለዋል ተብሏል። የኅብረት ሥራ ኮሚሽን ፖሊሲን ከማውጣት ጋር በተያያዘ ያሉትን ችግሮች ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጋር በመነጋገር የመጨረሻውን ውሳኔ ለቋሚ ኮሚቴው ሪፖርት እንዲቀርብ ሲሉ ያሳሰቡት ደግሞ፣ የተከበሩ ሱመያ ደሳለው መሆናቸውን ዘገባው ያሳያል። የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አብዱ ሙሃመድ በበኩላቸው፣ ማኅበራት ያሉበትን ደረጃ በመለየት እና በጥናት በማረጋገጥ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት በትኩረት እየተሰራ መሆኑን ለቋሚ ኮሚቴው አስረድተውል፡፡

የወሩ ኹለተኛ ሪፖርት አቅራቢ የነበረው፣ **የኢፌድሪ መከላከያ ሚኒስቴር** ነበር። ተቋሙ፣ የ2017 ዓ.ም. የዐሥር ወራት የዕቅድ አፈፃፀሙን ለምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ባቀረበበት ወቅት የተገኙት የኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ነጎዎ፣ መከላከያ ስራዊቱ የውስጥ ሰላምን ለማስፈን፣ አገርን ለማረጋጋት፣ የውጭ ወራሪን ለመመከት እና ሉዓላዊነትን ለማስከበር የሚያሳየው ቁርጠኝነት የሚበረታታ እንደሆነ ገልጸዋል ተብሏል። ዲማ አክለውም፣ በአገሪቱ የሚስተዋሉ ጥቃቅን ግጭቶች በክልሎች እንዲፈቱ እና መከላከያ ሠራዊቱ ወደ ዋና ተልኮው ተመልሶ የተጣለበትን አገራዊ ኃላፊነት የበለጠ መወጣት እንዲችል ትኩረት መደረግ እንዳለበት መናገራቸው ተዘግቧል።

የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት ኢንጂነር አይሻ መሐመድ በበኩላቸው፣ የተቋሙን የማስፈጸም አቅም በማጎልበት አገር እና ሕዝብን ከማንኛውም ጥቃት የመከላከል ሥራ በትኩረት እየተሰራ እንደሆነ ሲናገሩ ተስተውለዋል። ተዓማኒነት ያለው ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ ወታደራዊ የፍትሕ ዳኝነት እየተሰጠ ነው ያሉት ሚንስትሯ፣ በሌላ በኩል የሠራዊቱን አስተማማኝ የቁሳቁስ ክምችት ማሟላት እንደተቻለ ለቋሚ ኮሚቴው ገልጸዋል።

የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ በበኩላቸው፣ መከላከያ ሠራዊቱ የምሥራቅ አፍሪካን ሰላምና ደህንነት በዘላቂነት ለማረጋገጥ በትኩረት እየሰራ መሆኑን አስገንዝበዋል ተብሏል። ኢትዮጵያ ወደብ እንድታገኝ፣ ከቀጠናው አገራት ጋር በትብብር ለመስራት እና በጋራ ለመበልጸግ ያላሳለሰ ጥረት እያደረገች እንደሆነ የተቀሱት ፊልድ ማርሻሉ፣ ኢትዮጵያ የባሕር በር እንዲኖራት አቅደን ነው ብቃት ያለው የባሕር ኃይል እየገነባን ያለነው ብለዋል ተብሏል፤ አሁን ላይም፣ በየብስም ሆነ በባሕር የሚቃጡ ትንኮሳዎችን የሚመክት ሠራዊት መገንባቱን ያነሱት ኢታማዦር ሹሙ፣ ክልሎች በራሳቸው አቅም ሰላማቸውን እንዲያረጋግጡ እና መከላከያ ሠራዊቱ ወደ ዋና ተልዕኮው እንዲዞር በትኩረት እየተሰራ መሆኑን መናገራቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ **የኢትዮጵያ ሎተሪ አገልግሎት** በክዋኔ ኦዲት ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት ማስተካከያ ሊያደርግ እንደሚገባ ያሳሰበበት ሁነት ደግሞ ሣስተኛው የወሩ የእንደራሴዎቹ የተቋም ቁጥጥር ክንውን ነበር። በተቋሙ የእድል ሎተሪ ፈቃድ አሰጣጥ እና ገቢ አሰባሰብ ውጤታማነት ዙሪያ ያሉበትን የክዋኔ ኦዲት ግኝቶች በተመለከተ፣ ቋሚ ኮሚቴው ከባለድርሻ አካላት ጋር ይፋዊ የውይይት መድረክ አካሂዷል።

በውይይቱ ወቅት ቋሚ ኮሚቴው በእድል ሎተሪ ከፈቃድ አሰጣጥ እና እድሳት፣ ከክትትል እና ቁጥጥር እና ሕገ-ወጥነትን ከመከላከል አኳያ በተለዩ የክዋኔ ኦዲት ግኝቶች ላይ ተቋሙ ተጨባጭ የእርምት ማስተካከያ አለማድረጉን መግለፁ ተሰምቷል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ አራሬ ሞሲሳ፣ የኢትዮጵያ ሎተሪ አገልግሎት ያሉበትን የክዋኔ ኦዲት ግኝቶችን በየዘርፉ ለይቶ መፍታት እንዲችል ቅድሚያ ተገቢውን የአሰራር ሥርዓት ሊዘረጋ እንደሚገባ አሳስበዋል ተብሏል። ከዚህ ባለፈም፣ በገቢዎች ሚኒስቴር እና በሎተሪ አገልገሎቱ መካከል ያለው የሕግ አለመጣጣም እንዲቀረፍ፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ፣ ፍትሕ ሚኒስቴር፣ ፕላን እና ልማት ሚኒስቴር በቅንጅት ሰርተው ውጤቱን በ2018 ዓ.ም. መስከረም መጨረሻ ላይ ለቋሚ ኮሚቴው ሪፖርት ሊያቀርቡ እንደሚገባ አቅጣጫ መሰጠቱትን የምክር ቤቱ ዘገባ ያሳያል።

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ክብርት መሰረት ዳምጤ፣ የኢትዮጵያ ሎተሪ አገልግሎት በተለዩ የክዋኔ ኦዲት ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት ማስተካከያ መውሰድ እንዳለበት ጠቁመው፣ በሕገ-ወጦች ላይ ከፈቃድ ስረዛ ባለፈ ተጠያቂነት ሊረጋገጥ እንደሚገባ አመላክተዋል። የኢትዮጵያ ሎተሪ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈፃሚ ቤዛ ግርማ በበኩላቸው፣ የክዋኔ ኦዲት ግኝቶችን ለማረም ጥረት እየተደረ መሆኑን ገልጸው፣ የተቋሙን ገቢ የመሰብሰብ አቅም ከአራት ሚሊየን ወደ 2.2 ቢሊየን ማሳደግ እንደተቻለ ለኮሚቴው አባላት ነግረዋቸዋል ተብሏል።

ሰኔ 11 ላይ የዐሥራ አንድ ወራት የሥራ አፈፃፀሙን ለምክር ቤቱ የማቅረብ ተራው የነበረው ደግሞ፣ **የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር** ነበር። የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን የዐሥራ አንድ ወራት ሪፖርት ያደመጠው፣ በምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ነጎዎ፣ ሚኒስቴሩ በሚያደርጋቸው ዘርፈ-ብዙ ግንኙነቶች ላይ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እና የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ የሕግ ማዕቀፎች እንዲከበሩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባዋል ብለዋል ተብሏል፡፡ ኢትዮጵያ የተለያዩ ዓለም ዓቀፍዊ እና አህጉራዊ ተቋማት መስራች እና አባል አገር መሆኗን ያስታወሱት ሰብሳቢው፣ ኢትዮጵያዊያን በእነዚህ ተቋማት በሚገኙ የተለያዩ እርከኖች ላይ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ መስራት እንደሚገባም ተናግረዋል፡፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትሩ ክቡር ዶ.ር. ጌዲዮን ጢሞቲዮስ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ ከጎረቤት አገራት ጋር ያላት በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ትብብር ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማድረግ በከፍተኛ ደረጃ የጉብኝት ልውውጦች፣ የጋራ ኮሚሽን ስብሰባዎችን እና የፖለቲካ ምክክሮችን በማድረግ የሁለትዮሽ ግንኙነትን እና ቀጠናዊ ትስስርን ለማጠናከር የሚያስችሉ ሥራዎች መሰራታቸውን ለቋሚ ኮሚቴው ማብራራታቸውን መረጃው ይጠቁማል። ከጎረቤት አገራት ጋር ያለውን የኤሌክትሪክ ትስስር ለማጠናከር ከሶማሌ-ላንድ ጋር ሕጋዊ ማዕቀፎችን ለማበጀት መሥሪያ ቤታቸው እየጣረ እንደሆነ ያነሱት ጌዲዮን፣ በ21 አገራት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ከሚገኙ ዜጎች ውስጥ ከ131 ሺህ በላይ ዜጎች ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ተደርገዋል ማለታቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ይጠቁማል።

ኢትዮጵያ ባለፉት ዐሥራ አንድ ወራት ከሰባት ቢሊየን ዶላር በላይ የውጪ ንግድ ማገኘቷ የተሰማበት **የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር** የዐሥራ አንድ ወራት ሪፖርትም፣ በወርኃ ሰኔ የተከወነ አንዱ የእንደራሴዎቹ የተቋማት ክትትል ነበር። የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትሩ ዶ.ር. ካሣሁን ጎፌ፣ የሚመሩት ተቋም በበጀት ዓመቱ ዐሥራ አንድ ወራት ያከናወናቸውን ዋና ዋና ተግባራት በተመለከተ ለምክር ቤቱ አባላት ሪፖርት እና ማብራሪያ አቅርበው ነበር።

ከግብርና ምርቶች፣ ከማኑፋክቸሪንግ፣ ከማዕድን፣ ከኤሌክትሪክ እና ከሌሎች ንዑስ የኢኮኖሚ ዘርፎች በአጠቃላይ 4.59 ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 7.21 ቢሊዮን ዶላር ማሳካት ስለመቻሉ ገልጸዋል። የተገኘው ገቢ ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ3.96 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ብልጫ ስለማሳየቱ ያነሱት ሚኒስትሩ፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከወጪ ንግድ ገቢ አፈጻጸም ከ8 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ እንደሚጠበቅ ተናግረዋል ተብሏል። ይኸን የንግድን እና ቱሪዝም ሪፖርት ያደመጠው በምክር ቤቱ የንግድ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የቀረበለትን ሪፖርት በመገምገም በቀጣይ ትኩረት በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ግብረ መልስ አቅርቧል ተብሏል፡፡ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ አይሻ ያህያ፣ የፍጆታ ዕቃዎች አቅርቦት እና ስርጭትን በማረጋገጥ እና ሕገ-ወጥ የዋጋ ንረትን በመቆጣጠር ማኅበረሰቡ ላይ የሚደርስ የኑሮ ውድነት ጫናን ለመቀነስ ተጨማሪ ስራዎች እንደሚያስፈልጉ አስገንዝበዋል፡፡

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ባካሄደው 39ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ **የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት** የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የ2016 ዓ.ም. በጀት ዓመት የሂሳብ የፋይናንሽያል ሕጋዊነት እና የክዋኔ ኦዲት ሪፖርትን የገመገመበት መድረክም አንዱ ክንውኑ ነበር። የተከበሩ አፈ-ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎም፣ በዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት መሰረት፣ የኦዲት ግኝት ክፍተት ባሳዩ ተቋማት ላይ አስፈላጊውን አሥተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ምክር ቤቱ የበኩሉን ድርሻ እንደሚወጣ መናገራቸው ተሰምቷል፡፡ አፈ-ጉባኤው ለጥቀውም፣ የምክር ቤቱ የመንግስት ወጪ፣ አሥተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች እና የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴዎች አቅደው አስፈላጊውን ቁጥጥር በማድረግ የኦዲት ግኝቶች ክፍተቶችን ለማረም በትኩረት እንዲሰሩ ሲሉ አስገንዝበዋል ተብሏል፡፡

የመንግስት ወጪ፣ አሥተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዋ የተከበሩ ዶ.ር. የሺ እመቤት ደምሴ በበኩላቸው፣ የባለበጀት መሥሪያ ቤቶች የኦዲት ግኝት ክፍተቶችን ለማረም እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች መኖራቸውን ጠቁመው፣ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የተቋማትን የማስፈጸም አቅም በማሳደግ የኦዲት ክፍተቶችን ለማረም በትኩረት መስራት እንዳለበት ማስገንዘባቸውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ያሳያል። ከዚኹ ጋር በተያያዘ የምክር ቤቱ መረጃ፣ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሠረተ ዳምጤ ባቀረቡት የፌዴራል መሥሪያ ቤቶች የ2016 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት፣ ተቋማት መመሪያን ሳይከተሉ ከ404 ነጥብ 7 ሚሊዮን ብር በላይ ግዢ መፈፀማቸውን ተናግረዋል። ይኸንኑ የኦዲት ሪፖርት ተከትሎም፣ ታገሰ ጫፎ፣ የኦዲት እርምት በማያደርጉ ተቋማት ላይ ሕጋዊ፣ ፓለቲካዊ እና አሥተዳደራዊ እርምጃ እንደሚወሰድ ማስጠንቀቃቸው ተዘግቧል።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በ4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን በ40ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ **የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴርን** የ 2017 ዓ.ም. በጀት ዓመት የ11 ወራት የዕቅድ አፈፃጸም ሪፖርትን ያደመጠበት ኹነትም፣ ሌላይኛው የተቋማት ቁጥጥር የወርኃ ሰኔ ክንውኑ ነበር። የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. አለሙ ስሜ፣ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸውን የዕቅድ አፈፃጸም ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት፣ እንደራሴዎቹ በየካቲት ወር 2017 ዓ.ም ወደ 'ምርጫ ክልላቸው በሄዱበት ወቅት ከመንገድ ደህንነት፣ ከሕዝብ ትራንስፖርት አቅርቦት፣ ከትራንስፖርት ታሪፍ እና በሕገ-ወጥ ኬላዎች ዙሪያ በተያያዘ ከኅብረተሰቡ ለተነሱ 46 ለሚሆኑ ጥያቄዎች ምላሽ መሰጠቱን ገልጸዋል ተብሏል። ሚኒስትሩ አክለውም፣ በአገር አቀፍ ደረጃ 913 ሚሊየን ሕዝብ ለማጓጓዝ ታቅዶ 960 ሚሊየን ሕዝብ በማጓጓዝ ከዕቅድ በላይ መፈጸም መቻሉን ለእንደራሴዎቹ ነግረዋቸዋል። የአንድ አገር አቋራጭ አውቶብስ አማካይ ዓመታዊ ኪሎ ሜትር ሽፋን በዓመቱ 107 ሺህ ኪሎ ሜትር ለማድረስ ታቅዶ 105 ሺህ ኪሎ ሜትር በማድረስ ውጤታማ አፈጻጸም መመዝገቡንም ሚኒስትር አለሙ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

በትራንስፖርት ዘርፍ አሁንም በርካታ ያልተፈቱ ችግሮች መኖራቸውን ያነሱት እንደራሴዎቹ በበኩላቸው፣ የትራፊክ አደጋ ከመቀነስ ይልቅ መባባሱን፣ የሞጆ ደረቅ ወደብ ሥራ መጓተት፣ የትራፊክ ፍሰቱን የሚያስተጓጉሉ ሕገ ወጥ ኬላዎች መኖር እና ለኤሌክትሪክ መኪኖች በቂ የቻርጅ ማድረጊያ ቦታ አለመኖርን በዋናነት ጨምረው መጥቀሳቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ይጠቁማል። ለመሰል ጥያቄዎች ምላሽ የሰጡት ሚኒስትሩ አለሙ ስሜ፣ ሕገ ወጥ ኬላዎችን በተመለከተ ችግሩ ሁሉንም አካል የሚጎዳ በመሆኑ በጉባኤ ጭምር ተገምግሞ መፍትሔ እንዲሰጥበት ቢደረግም፣ አሁንም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ችግሩ መኖሩን መሥሪያ ቤታቸው እንደሚያውቅ ጠቅሰዋል። በምክር ቤቱ የከተማ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴም፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የትራንስፖርት ዘርፉን ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ እና ተደራሽ ለማድረግ እያከናወናቸው ያሉ ተግባራትን ይበልጥ ማጠናከር እንዳለበት አሳሰቧል ተብሏል፡፡

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ኑ/ር መሐመድ አብደም፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ያከናወናቸውን ውጤታማ ተግባራት የበለጠ ለማስፋት እና ቀጣይነት እንዲኖራቸው፣ ደካማ አፈፃጸም የታየባቸውን ተግባራት እንዲታረሙ በማድረግ ለ2018 በጀት ዓመት እቅድ ግብዓት አድርጎ መውሰድ እንደሚገባ ማሳሰባቸውን ዘገባው ያመለክታል።

ሰኔ ሦስተኛ አጋማሽ ላይ የ2017 ዓ.ም. የዐሥራ አንድ ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱን እንዲያቀርብ የተጠራው ደግሞ **የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ** ነበር። የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ደሣለኝ ወዳጄ፣ በአገር ደረጃ የገንዘብ ፖሊሲ ሪፎርሙ የተገኙ ውጤቶች አበረታች መሆናቸውን ጠቁመው፣ ብሔራዊ ባንክ ተልዕኮውን በአግባቡ ለመወጣት የተጀመሩ ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አስገንዝበዋል ተብሏል፡፡ ባንኩ የውጭ ምንዛሪ አሥተዳደር ሥርዓት በገበያ እንዲወሰን ማድረጉ የሚበረታታ እና ተጨባጭ ለውጦች የታየበት ሥራ መሆኑን የጠቀሱት ሰብሳቢው፣ የውጭ ባንኮች ወደ አገር ውስጥ ገብተው እንዲሳተፉ ማድረጉም የውጭ ባለሀብቶችን በመሳብ ለአገር ውስጥ የካፒታል ገበያ እንዲያድግ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም ዓለምአየሁ በበኩላቸው፣ የገንዘብ ፖሊሲ ማሻሻያው ለአገር ዕድገት ወሳኝ ሚና እንዳለው አንስተው፣ የዲጂታል ግብይት ሥርዓት፣ የኤቲኤም እና የፖስ ማሽኖች ቁጥር እያደገ መምጣቱ የሚበረታታ ተግባር መሆኑን ተናግረዋል ሲል ዘገባው ጠቅሷቸዋል። የብሔራዊ ባንክ ገዥው ክቡር አቶ ማሞ እስመለዓለም ምሕረቱ በበኩላቸው፣ በገንዘብ ፖሊሲ አፈጻጸም፣ በውጪ ምንዛሪ አሥተዳደር እና በፋይናንስ ዘርፍ እንቅስቃሴ ባለፉት ዐሥራ አንድ ወራት አበረታች ውጤት መመዝገቡን ለቋሚ ኮሚቴው አባላት ነግረዋቸዋል። ማሞ አክለውም፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ ክምችት ከነበረበት ሦስት እጥፍ ማሳደግ መቻሉን ተናግረዋል።

በወርኃ ሰኔ 23ኛው ቀን፣ የዐሥራ አንድ ወራት የሥራ አፈፃፀሙን እንዲያቀርብ የተጠራው፣ **የገቢዎች ሚኒስቴር** ሲሆን፣ ሪፖርቱን የገመገመው የምክር ቤቱ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴም፣ ተቋሙ የተሻለ አፈፃፀም ማሳየቱን ገልጿል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ፣ ገቢዎች ሚኒስቴር እና በስሩ የሚገኘው ጉሙሩክ ኮሚሽን በአንድ ላይ በመሆን በአገሪቱ ገቢ ላይ ትልቅ ሚናና ድርሻ ያላቸው ተቋማት እንደሆኑ አስረድተዋል፡፡

ተቋማቱ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የአገሪቱን የ10 ዓመት እቅድ እንዲሁም የመካከለኛ ዘመን እቅድ መነሻ በማድረግ የ2017 ዓመታዊ በጀት እቅድ አዘጋጅተው ወደ ተግባር እንደገቡ መደረጉን እና በ11 ወራቱም ጥሩ ውጤት ያስመዘገቡ መሆኑን ደሳለኝ ጨምረው መናገራቸውን ዘገባው ያሳያል።

የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት አይናለም ንጉሴም፣ የቋሚ ኮሚቴው አባላት ላነሱላቸው ጥያቄዎች ማብራሪያ እና ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በ2017 በጀት ዓመት ከአገር ውስጥ እና ከውጭ ንግድ ቀረጥ በ11 ወራት ውስጥ 814.70 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 815.34 ቢሊየን ብር መሰብሰብ መቻሉን ያነሱት አይናለም፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ለመሰብሰብ የተያዘው 900.27 ቢሊዮን ብር እንደሚሳካ ታሳቢ ተደርጓል ብለዋል።

አይናለም አያይዘውም፣ በ2017 በጀት ዓመት የውጭ ንግድ እና ታክስ የገቢ አፈጻጸም 403 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 414.44 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ መቻሉን ገልጸው፣ አፈጻጸሙ ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ከተሰበሰበው የ116.96% ብልጫ እንዳለውም ተናግረዋል ተብሏል፡፡ በመጨረሻም ሚኒስትሯ፣ በየቦታው የተተከሉ ሕገ-ወጥ ኬላዎች መብዛት እና በንግድ ማኅበረሰቡ ላይ ጫና እያሳደሩ መሆኑን መናገራቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል።

## የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ወርኃ ሰኔን ያጠናቀቀው ሕግጋትን በማውጣት እና የተቋማትን ሪፖርቶች በማድመጥ ብቻም አይደለም፤ ከዚያ ተሻግሮም በዛ ያሉ ተቋማትን በተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎቹ በኩል ሲጎበኝ፣ ከኹለት ዐሥርት የማያንሱ የመስክ ጉብኝቶችንም አድርጓል።

## የተቋማቱ ጉብኝቶች

እንደራሴዎቹ፣ በወርኃ ሰኔ ከጎበኟቸው ተቋማት መካከል በቀዳሚነት ማሳያ የሚሆነው፣ **የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ነው**። ተቋሙን የጎበኘው በምክር ቤቱ የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፣ ኮሚቴው ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ጋር ባደረገው ውይይት፣ ሠራተኛውን ለማበረታታት የሸማች ማኅበር በማቋቋም በቅናሽ ዋጋ ሸቀጦችን እንዲገዙ መድረጉን ተመልክቷል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መስፍን ዳኜ በበኩላቸው፣ በሠራተኞች የተነሱ ጉዳዮች መፈታት እንዳለባቸው እና እናቶች ተረጋግተው ሥራቸውን እንዲሰሩ የሕጻናት ማቆያ መገንባት እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡ የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታው ክቡር ተስፋዬ ይገዙ በበኩላቸው፣ ግዥ ሰኔ እና ግንቦትን ጠብቆ እንዳይገዛ በጥንቃቄ መመራቱን መናገራቸውን ከተቋሙ የመስክ ምልከታ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

ሌላይኛው የወሩ ማሳያ ተጎብኚ ተቋም፣ **የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል** ነበር። ሰኔ ኹለት ወደ ሆስፒታሉ የደረሱት በምክር ቤቱ የሰው ሀብት ልማት፣ ስራ ስምሪት ና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የሆስፒታሉን ከፍተኛ አመራሮችን ከማነጋገራቸው ባለፈ፣ የስፔሻላይዝድ ሆስፒታሉን የተለያዩ የህክምና ክፍሎችን እና በግንባታ ላይ የሚገኘውን የጋዜጠኝነትና ሥነ-ተግባቦት የትምህርት ክፍል ሕንጻንም ተዘዋውረው ተመልክተዋል ተብሏል። በመንገድ ዳር እና ፊት ለፊት የሚገነቡ የሕንፃ ክፍሎች ለንግድ ሥራ እንዲውሉ በማድረግ የዩኒቨርሲቲውን የገንዘብ አቅም የሚያጠናክር እና ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው የራሱን የገንዘብ ምንጭ የማሳደግ ጥሩ ጅማሬ መሆኑንም የቋሚ ኮሚቴው አባላት መግለፃቸውን ዘገባው ጠቅሷል።

በዚኹ ሽፋን በሰጠነው ወርኃ ሰኔ፣ በምክር ቤቱ የመንግስት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተጎበኘው **የፌደራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትም** አንዱ የወሩ ማሳያ የመስክ ጉብኝት ክንውን ነበር። በበጀት ዓመቱ ነቀፌታ ያለበት የኦዲት ግኝት አስተያየት ለኢትዮጵያ አካል ድጋፍ አገልግሎት፣ ለፌደራል ፖሊስ ዩኒቨርስቲ እና ለመንገድ ደህንነት እና መድን ፈንድ አገልግሎት ተቋማት የተሰጠ መሆኑን በመስክ ጉብኝቱ የጠቀሰው ኮሚቴው፣ ከዚህ ባለፈም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እና በበላይ የሥራ ኃላፊዎች ላይም የገንዘብ ቅጣት መጣሉን አሳውቋል ተብሏል፡፡ በተጨማሪም ለጋምቤላ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲዎች እና ለውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት እንዲኹም ለኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት ጭምር የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ተግባር መሰራቱንም ኮሚቴው ተናግሯል ተብሏል፡፡ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. የሺ እመቤት ደምሴም፣ የፎረሙ ሚና የማይተካ ለውጥ እያመጣ መሆኑን አስገንዝበው፤ ዋና ዓላማው መቅጣት ሳይሆን አሰራርን በማዘመን እና ተጠያቂነትን ለማስፈን እንደሆነ ገልጸዋል ሲል ዘገባው ጠቅሷቸዋል።

በዚኹ ሰኔ ወር፣ በእንደራሴዎቹ ከተጎበኙ ተቋማት መካከል የመጨረሻ ማሳያ ሊሆን የሚችለው **የገቢዎች ሚኒስቴር** ነው። ተቋሙ የጎበኙት በምክር ቤቱ የመንግስት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር ተወካዮች ሲሆኑ፤ ‘ነርሱም፣ ተቋሙ የ2014/15 የክዋኔ ኦዲት ግኝት ላይ አበረታች እርምት መውሰዱን ተናግረዋል ተብሏል። በቀጣይም የታክስ ዕዳ መረጃ አያያዝ ሞጁል ወደ ሙሉ ትግበራ ለመገባት ግልጽ የጊዜ ገደብ ተቀምጦለት ሊተገበር የሚገባ እና ሌሎች ተቋማት የሚጠቀሟቸውን ቴክኖሎጂዎች ከተቋሙ ጋር የሚተሳሰሩበት ሁኔታዎች ማመቻቸት እንደሚገባ በቋሚ ኮሚቴው ግብረ መልስ መመላከቱን መረጃው ያሳያል፡፡ የግብር ከፋዮች ወቅታዊ ሀብት እና ንብረት የሚመዘገብበት አሠራርም ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ተመላክቷል ተብሏል፡፡

ተቋሙ በቀጣይ በኦዲት ሪፖርቱ የተመላከቱ ግኝቶችን ለቅሞ በመያዝ እና የዕቅድ አካል ማድረግ እንደሚገባው እና የተወሰዱ ማሻሻያዎችን በየ3 ወሩ ለቋሚ ኮሚቴው ሪፖርት መላክ እንደሚጠበቅበት የኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. የሺ እመቤት ማሳሰባቸውን መረጃው ይጠቁማል። የገቢዎች ሚኒስትሯ ዓይናለም ንጉሤ በበኩላቸው፣ የገቢዎች ሚኒስቴር የገቢ አሰባሰብ ሂደቱን ለማሳደግ ዘርፈ-ብዙ ተግባራትን እያከናወነ እንደሚገኝ እና በቀጣይም ይህንኑ አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል ተብሏል።

## የመስክ ጉብኝቶች



በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ልማት ድርጅቶች ቋሚ ኮሚቴ በጋምቤላ ክልል ያደረገው የመስክ ምልከታ በከፊል

በዚኽ ዕትም በሸፈንነው ሰኔ ወር፣ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ካደረጋቸው የመስክ ጉብኝቶች መካከል፣ በቀን ምጣኔ በቀዳሚነት የሚነሳው የዳሰነች ማኅበረሰብን ሕልውና አስመልክቶ በምክር ቤቱ የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያደረገው ጉብኝት ነው። ቋሚ ኮሚቴው፣ **በደቡብ ኦሞ ዞን በዳሰነች ወረዳ** በመገኘት በኦሞ ወንዝ እና በቱርካና ሐይቅ ሙላት ምክንያት የተፈናቀሉ አርብቶ አደሮችን ተመልክቷል፡፡ ችግሩን ለመፍታት የሚደረጉ ጊዜያዊ መፍትሔዎችን ተዘዋውሮ የተመለከተው ቋሚ ኮሚቴው፣ በቀጣይ መደረግ በሚገባቸው ዘላቂ መፍትሔዎች ዙሪያ ከወረዳው የሥራ ሃላፊዎች ጋር ውይይት ማድረጉን ዘገባዎቹ ጠቁመዋል፡፡ የቋሚ ኮሚቴው አባላት በውይይቱ ወቅት እንደገለጹት፣ የአካባቢው አርብቶ አደሮች በኦሞ ወንዝ እና በቱርካና ሐይቅ ሙላት ምክንያት ከሚኖሩበት ቀዬ እየተፈናቀሉ እና መንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት የተገነቡ የተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በውኃ ሙላቱ ምክንያት ከአገልግሎት ውጭ እንደሆኑ መታዘባቸውን ተናግረዋል ተብሏል፡፡ ለውኃ ሙላት ችግሩ ጊዜያዊ መፍትሄ ከመስጠት ጎን ለጎን፣ የአርብቶ-አደሩን ስቃይ የሚቀንስ፣ እንዲሁም የተቋማትን ውድመት በዘላቂነት መከላከል የሚያስችል ሥር ነቀል ጥናት ማድረግ ይገባል ማለታቸውን ተዘግቧል።

የኮሜቲው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. አወቀ አምዛዬ በበኩላቸው፣ የአገሪቱ ኢኮኖሚ በአካባቢው ከሚገኘው ከፍተኛ ሀብት የሚደገፍበትን ሁኔታ መፍጠር እንደሚገባ መናገራቸው ተሰምቷል። የዳሰነች ወረዳ አሥተዳደሪው ታደለ ሀቴም፣ በቱርካና እና በኦሞ ወንዝ ሙላት ምክንያት ከ79 ሺህ በላይ የወረዳው አርብቶ-አደሮች መፈናቀላቸውን በዚያ ላገኟቸው የኮሚቴው አባላት ነግረዋቸዋል። ለችግሩ ዘላቂ የሆነ መፍትሔ ባለመበጀቱ ምክንያት ለሦስተኛ ጊዜ የተፈናቀሉ አርብቶ አደሮች መኖራቸውን ጨምረው የገለጹት አሥተደዳሪው፣ ከተማው ሙሉ በሙሉ የመዋጥ አደጋ ተጋርጦበታል ብለዋል፡፡ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ልማት ቢሮ ኃላፊው ኢካል ነትሪ በበኩላቸው፣ ክልሉ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የዳሰነች ከተማን እና በአካባቢው የሰፈሩትን አርብቶ አደሮች ሕይወት ለማዳን ጊዜያዊ የአፈር ድልደላ እየተሰራ መሆኑን ለኮሚቴው አባላት ጠቅሰውላቸዋል።



በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ልማት ድርጅቶች ቋሚ ኮሚቴ በጋምቤላ ክልል ወደ ጋምቤላ ክልል ባቀናበት ወቅት የክልሉ ርዕሰ መስተዳደር የተከበሩ ወ/ሮ አለሚቱ ኡመድ እና ከፍተኛ የክልሉ አመራሮች ተቀብለው ሲያነጋግሩዋቸው።

በሰኔ የመጀመሪያ ሳምንት መገባደጃ ላይ በእንደራሴዎቹ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ቋሚ ኮሚቴ የመጎብኘት ዕጣ የደረሳት ደግሞ የድንበር መሬቷ **ጋምቤላ** ነበረች። **በጎግ ወረዳ** የሚገኙትን የእርሻ ልማቶች ላይ የተዘሩትን የበቆሎ፣ የሰሊጥ እንዲሁም የበርበሬ ችግኝ እና በመጋዘን ላይ የተከማቹ ምርቶችን የጎበኘው ቋሚ ኮሚቴው፣ **በኢታንግ ልዩ ወረዳ** ዋንኬ ቀበሌ አኩላ መንደር የሚገኘውን የሐይሌ የማሾ፣ የማሽላ፣ የበቆሎ እንዲሁም ሌሎች ተዘማጅ የግብርና ልማቶች ላይ የመስክ ምልከታ ማድረጉን የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል።

ይኸው ኮሚቴም፣ ከኹለት ቀናት በኋላ ወደ **አፄ ዞን** በመሄድ፣ በእርሻ ልማት የተሰማሩት ባለሀብቶች ሥራዎችን በማስመልከት፣ የጋምቤላ ዲስትሪክት እና ቅርንጫፍ ልማት ባንክ ብድር ከማመቻቸት እና ልማቱ ይበልጥ እንዲሳለጥ እያደረገ ያለው ሚና ምን እንደሚመስል መመልከት መቻሉን ገልጿል ተብሏል። አልፎ አልፎ በተከማቹ ንብረቶች ላይ ዝርፊያ እየተከሰተ ስለሆነ ተገቢው ጨረታ ወጥቶ ንብረቶቹ እስኪሸጡ ድረስ፣ የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን በልዩ ድጋፍ መስራት እንደሚገባው እና አንዳንድ ባለሀብቶች ተበድረው የወሰዱትን ብድር እንዲመልሱ አመራሩ ከልማት ባንኩ ጋር በመሆን መስራት እንደሚጠበቅባቸውም መናገሩን ከመስክ ምልከታው የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

ሰኔ 18 2017 ዓ.ም. ወደ **አማራ ክልል ዋና ከተማ ባሕር ዳር** የደረሱት የምክር ቤቱ የከተማ እና መሠረተ ልማት እና የመንግስት ልማት ድርጅቶች እንዲሁም የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴዎች፣ የከትማይቱን የኮሪደር ልማት ጎብኝተዋል። ጥምር ኮሚቴው ከተለያዩ ተቋማት ኃላፊዎች ጋር የመግቢያ ውይይት ካደረገ በኋላ፣ የባሕር ዳር የኮሪዶር ልማት የግንባታ ሂደት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ እና በከተማዋ ሕዝብ ተሳትፎ ጭምር የለሙ መዝናኛዎችን ተዘዋውሮ ጎብኝቷል ተብሏል። የጥምር ኮሚቴው አስተባባሪ የተከበሩ መስፍን ዳኜም፣ ባሕር ዳር ከተማን ለማስዋብ ጣናን በማስተሳሰር የተሰሩ የኮሪዶር ልማቶች ተጨባጭ ውጤት የታየባቸው እና የአመራሩን የመፈጸም አቅም እና ቁርጠኝነት የሚያመላክቱ መሆናቸውን መግለፃቸውን ከመስክ ምልክታው የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

በወርኃ ሰኔ እንደራሴዎቹ ከከወኗቸው የመስክ ምልከታዎች መካከል ሳይነሳ የማያልፈው፣ በምክር ቤቱ የግብርና ጉዳዮች እና የኢንዱስትሪ እና ማዕድን ጉዳዮች ጥምር ኮሚቴዎች ሲዳማን የጎበኙበት ሁነት ነው። በ**ሲዳማ** ክልል የሚገኘው የግብርና ኢንዱስትሪ ዘርፉ እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል የተመለከተው ጥምር ኮሚቴው፣ በመስክ ፍተሻው የተረጋገጡ እና ሊጠናከሩ እንዲሁም ሊታረሙ ይገባቸዋል ያላቸውን ዝርዝር ነጥቦች ለሚመለከታቸው የክልሉ የኢንዱስትሪ እና የግብርና ቢሮ ኃላፊዎች እንዲሁም ለባለድርሻ አካላቱ አቅርቧል ተብሏል። በዚህም መሰረት ኮሚቴው የአግሮ ኢንዱስትሪ ዘርፉን ውጤታማነትን ዘላቂ ለማድረግ የመሠረተ ልማት አቅርቦት መኖሩ፣ ከዘርፉ አመራር እና ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ማስፈን መቻሉ፣ በማምረት ላይ ያሉ ኢንዱስትሪዎች የገበያ ችግር አለመኖር በአዎንታዊ መንገድ የተስተዋሉ መሆናቸውን መግለፁ ተዘግቧል። እንዲሁም በምልከታው ከተፈተሹ ኢንዱስትሪዎች አብዛኛዎቹ፣ የተቀናጀ የግብርና ኢንዱስትሪ ፓርክ ማኅበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አኳያ ያሉ ተግባራት ጠንካራ አፈፃፀሞች መሆናቸውም በዘኹ የመስክ ምልከታ ተነስቷል ተብሏል። ይሁን እንጂ ጥምር ኮሚቴው፣ የግብርና ኢንዱስትሪ ዘርፉን በማጠናከር የአገርን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ከውጭ የሚገቡ ለምርት ግብአትነት የሚውሉ ኬሚካሎች በአገር ውስጥ በአምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲመረቱ ድጋፍ በማድረግ በትኩረት ሊሰራበት ይገባል ማለቱም ተዘግቧል።

የሲዳማ ክልል የኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊው ጎሳዬ ጎዳና በበኩላቸው፣ በጥምር ኮሚቴው የተሰጠውን ግብረ-መልስ በመውሰድ የጋራ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ በቅንጅት የሚሰሩበት እንደሆነ ጠቅሰዋል ተብሏል። ክልሉን እየፈተነው ያለውን የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት በኢንዱስትሪ ዘርፉ ውጤታማነት ላይ ተፅዕኖ እንዳያሳድር የሚመለከተው አካል ሁሉ ርብርብ ሊያደርግበት እንደሚገባም ላገኟቸው የጥምር ኮሚቴው አባላት አንስተውላቸዋል። በመጨረሻም የጥምር ኮሚቴው ቡድን መሪ የተከበሩ ሙባረክ ኤልያስ፣ ኹሉም ባለድርሻ አካል የአገርን ምጣኔ ሀብት ለማሳደግ በሚሰራው ሥራ በግብርና ኢንዱስትሪ ዘርፉ ላይ ጥራትን በማስጠበቅ በትኩረት መስራት እንደሚገባ አሳስበው የኮሚቴዎቹ የሲዳማ የመስክ ምልከታ ተጠናቋል።

# የፓርላማ ዲፕሎማሲ

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በዚኽ ዓመቱ ዐሥረኛ ወር ውስጥ አንድ ፓርላመንታዊ የዲፕሎማሲ ሥራ ከውኗል።



የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ የደቡብ ኮሪያ ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ ጆ ሆ ያንግን ባወያዩበት ወቅት።

የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ የደቡብ ኮሪያ ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ ጆ ሆ ያንግን ያወያዩበት ኹነት ነው። በኢትዮጵያ የደቡብ ኮሪያ አምባሳደሩ ጂንግ ካንግን ጨምሮ፣ የደቡብ ኮርያ ምክር ቤት ልዑካን በተገኙበት በዚኽ ውይይት፣ በኹለቱ አገራት መካከል ያለው ረዥም ዘመናት ያስቆጠረ ዲፕሎማሲያዊ እና ዘርፈ ብዙ ግንኙነት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ታገሰ መናገራቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ያሳያል። ኢትዮጵያ በአፍሪካ ለመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት ምቹ ከሆኑ አገራት ቀዳሚ ናት ያሉት ታገሰ፣ የደቡብ ኮሪያ መንግሥት እና ባለሀብቶች በኢትዮጵያ መዋዕለ-ንዋያቸውን ለማፍሰስ ካሹ ኢትዮጵያ በሯ ክፍት ነው ብለዋልም ተብሏል።

ኢትዮጵያ የፋይናንስ እና የውጪ ምንዛሬ ሥርዓቷ ላይ ማሻሻያዎች በማድረግ ለመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት ምቹ በማድረግ ላይ እንደምትገኝ የጠቀሱት ታገሰ ጫፎ፣ የደቡብ ኮሪያ መንግሥት በትምህርት እና ሥልጠና አልፎም በህክምና እና ቴክኖሎጂ ዘርፎች እያደረገ ላለው ድጋፍ ምስጋናቸውን አቅርበዋል ተብሏል። ደቡብ ኮሪያ በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣ ትምህርትን በጥራት ለዜጎቿ ተደራሽ ለማድረግ የሄደችባቸው መንገዶች ተሞክሮ የሚወሰድባቸው መሆናቸውን ለልዑካን ቡድኑ ገልፀውላቸዋል።

የደቡብ ኮሪያው ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ ጆ ሆ ያንግ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ በኮሪያ ጦርነት ወቅት ባሳየችው አጋርነት የተነሳ በአፍሪካ ካሉ አገራት በተለየ ሁኔታ በደቡብ ኮሪያ መንግሥት እና ሕዝብ ዘንድ ቅድሚያ ይሰጣታል ብለዋል። የደቡብ ኮሪያ መንግሥት እና ተቋማት በትምህርት እና ሥልጠና እንዲኹም በህክምና፣ በቴክኖሎጂ እና ሌሎች ዘርፎች በኢትዮጵያ እያከናወኑ ያሉትን ሥራዎች አጠናክረው እንደሚቀጥሉ የጠቀሱት ያንግ፣ የኢትዮጵያውያ ወጣቶችን የትምህርት እና የሥራ ዕድል ፍላጎት ከግምት በማስገባት በኢትዮጵያ በሚገኙ ተቋማት የማስፋፊያ ሥራዎችን እየሰራን እንገኛለን ብለዋል ተብሏል። አፈ-ጉባኤው አክለውም፣ የደቡብ ኮሪያ መንግሥት የኹለቱን አገራት የፓርላማ ዲፕሎማሲ ግንኙነት ለማጠናከር ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለውም ተናግረዋል።

# እንደራሴዎቹ ስለ'ራሳቸው በ'ራሳቸው

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ ወርኃ ሰኔን ያጠናቀቁት ሕጋግት በማውጣት አልያም ተቋማትን በመጎብኘት ብቻም አልነበረም፤ ከዚኽ ተለምዷዊ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነታቸው ሻገር ብለውም፣ የራሳቸውን ምክር ቤት የ2017 ዓ.ም. በጀት ዓመት የዕቅድ ክንውን ሪፖርትን እና የ2018 ዓ.ም. በጀት ዓመት መሪ ዕቅድን ተንተርሰው ሰፋ ያሉ የ'ርስ በ'ርስ ውይይቶችን አድርገዋል።

ይኽ የዚኽኛው ዓመት የዕቅድ ክንውን እና የቀጣዩ ዓመት መሪ ዕቅድ ውይይት ላይ የተገኙት የተከበሩ አፈ-ጉባኤ ታገሰ ጫፎ፣ በ2017 በጀት ዓመት በሕግ ማውጣት፣ በክትትል እና ቁጥጥር፣ በፓርላማ ዲፕሎማሲ እንዲኹም በሕዝብ ውክልና ክንውኖች አመርቂ ሥራዎች መከናወናቸውን አንስተዋል። በውይይት መድረኩም፣ የ2017 ዓ.ም. በጀት ዓመት የዕቅድ ክንውን ሪፖርት እና የ2018 ዓ.ም. በጀት ዓመት መሪ ዕቅድ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት የሙያዊ ዘርፍ ምክትል ዋና ኃላፊ ዶ.ር. ንጉሤ መሸሻ አማካኝነት መቅረቡን የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል። ክብርት ምክትል አፈ-ጉባኤ ሎሚ በዶ በበኩላቸው፣ የ2017 በጀት ዓመት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታሪክ ከ40 በላይ መደበኛ ጉባዔዎች የተስተናገዱበት እና ሥራዎች በልዩ ትኩረት ሳይንጠባጠቡ የተሰሩበት ዓመት እንደሆነ ገልፀዋል ተብሏል።

የ2017 ዓ.ም. በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃጸም ሪፖርቱን ያቀረቡት ንጉሤ፣ የበጀት አመቱ የዕቅድ ክንውን ምክር ቤቱ በሕገ-መንግሥቱ በተሰጠው ሥልጣን እና ኃላፊነት መሠረት የሕግ ማውጣት፣ የክትትልና ቁጥጥር፣ የፓርላማ ዲፕሎማሲ እና የሕዝብ ውክልና ስራዎችን መነሻ በማድረግ እና በዕቅድ በማካተት የተከናወኑ አፈፃፀሞች እንደሆኑ ጠቁመዋል። ዶ.ር. ንጉሤ አክለውም፣ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን በተመለከተም በ13 ቋሚ ኮሚቴዎች የአስፈፃሚ ተቋማትን የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ ግብረ መልስ ለመስጠት ለ90 ተቋማት ታቅዶ፣ ለ98 ተቋማት የዕቅድ ግብረ -መልስ የመስጠት ስራ ተሰርቷል ማለታቸው ተዘግቧል። የ2018 ዓ.ም. በጀት ዓመት መሪ ዕቅድን ያቀረቡት ንጉሤ፣ የምክር ቤቱን ሕገ -መንግሥታዊ ኃላፊነት መሠረት በማድረግ ከ5 ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ እና ከ2017 የዕቅድ አፈፃፀም መነሻ በማድረግ የአገርን ቀጣይ ዕጣ ፈንታ የሚያስጠብቅ እና የሕዝብን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ዕቅድ መዘጋጀቱን ለእንደራሴዎቹ አብራርተውላቸዋል። ክብርት ምክትል አፈ-ጉባኤ ሎሚ በዶ በበኩላቸው፣ የ2017 በጀት ዓመት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት በርካታ ሥራዎች መከናወናቸውን አንስተዋል። ከዚህም ውስጥ ተቋማዊ አደረጃጀት እና ማሻሻያ አንዱ መሆኑን የጠቆሙት ሎሚ፣ ለዚህም ሥራ ስኬት የአደረጃጀት ኮሚቴው ከዕቅድ ዝግጅት ጀምሮ በየሳምንቱ ሥራዎችን በመገምገም ትልቅ ሥራ ሰርቷል ማለታቸውን ዘገባዎቹ ጠቅሰዋቸዋል።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት የአሥተዳደራዊ ዘርፍ ምክትል ዋና ኃላፊው ከረዩ ባናታ በበኩላቸው፣ የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድን የጋራ ከማድረግ ጀምሮ ሳምንታዊ፣ ወርኃዊ እና የሩብ ዓመት አፈፃፀም ሪፖርትን የመገምገም፣ በማሻሻያ ኮሚቴው እና የበላይ አመራሩ ክትትል እና ድጋፍ የነበሩበት መሆኑን አንስተዋል ተብሏል።

ከዚኹ መረጃ ጋር በተያያዘ፣ በወሩ ማጠናቀቂያ ዕለት የምክር ቤቱን የ2017 በጀት ዓመት የተጠቃለለ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ያቀረቡት ሎሚ በዶ፣ በምክር ቤቱ የአሠራር እና የአባላት ሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 አንቀጽ 53 (4) መሠረት፣ ረቂቅ ሕግጋት ለዝርዝር ምርመራ የተመራላቸው የቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ ከሕግ ምርመራ መሠረታዊ ነጥቦች አንጻር በተገቢ ሁኔታ መመርመር መቻላቸውን እንዳብራሩ ከምክር ቤት የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። ከዚኽ በተጨማሪም፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ የአረጋውያንን፣ የሴቶችን እና የሕፃናትን መብት የሚያስከበሩ መሆኑን፣ በመሠረታዊነት ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ እና ተፈጻሚ የሚያደርጋቸው አካላት መኖራቸውን በማረጋገጥ ሂደታቸውን ጠብቀው እንዲፀድቁ የማድረግ ሥራዎች መሰራታቸውን ምክትል አፈ-ጉባኤዋ ለአቻ እንደራሴዎቻቸው መናገራቸውን ዘገባዎቹ አመልክተዋል። በዚህ መሠረት በበጀት ዓመቱ ምክር ቤቱ ባካሄደው 43 መደበኛ እና 3 ልዩ ስብሰባዎች 56 ዐዋጆች ለምክር ቤቱ ኢኢቀርቡ፣ ከነዚህም ውስጥ 34ቱ ለቋሚ ኮሚቴዎች ተመርተው በሁለተኛ ንባብ ሲፀድቁ፣ 15ቱ ደግሞ ወደ ሁለተኛ ንባብ ተሸጋግሮ መፅደቃቸውን እና ከ2016 የተሸጋገሩትን 2 ዐዋጆችን ጨምሮ በአጠቃላይ 9 ዐዋጆች ወደ 2018 በጀት ዓመት መሻገራቸውን አብራርተዋል ተብሏል፡፡

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ በወሩ መጨረሻ ባካሄደው ስብሰባ የከወነው ተጨማሪ ጉዳይ፣ ምክር ቤቱ በ2017 በጀት ዓመት የፈጸማቸውን የፓርላማ ዲፕሎማሲ ሥራዎችን አስመልክቶ የቀረበለትን ሪፖርት የተመለከተው ነበር። በዚኹ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ የተናገሩት ምክትል አፈ-ጉባኤዋ ሎሚ በዶ፣ በዲፕሎማሲ መስክ በተሰራው ሥራ ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ የምግብ ዋስትና ራስን ለመቻልና የምግብ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ የተሠሩ ያሉ ሥራዎች በጥናት ተሰንዶ መረጃን ለምስራቅ አፍሪካ የግብርና ተቋማት ማቅረብ መቻሉን ገልፀዋል ተብሏል። የዲፕሎማሲ ስራዎችን ለማጠናከር ያግዝ ዘንድ በኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ዘርፍ ለምክር ቤት አባላት የአቅም ግንባታ ስልጠና መሰጠቱንም ሎሚ ጨምረው ጠቅሰዋል።

# ኢትዮጵያ ምን ተስማማች?

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አበይት ክንዋኔዎች መካልከል አንዱ አገሪቷ ከተለያዩ አገራት እና ዓለም ዓቀፍ ተቋማት ጋር ያደረገቻቸውን የብድር ስምምነቶችንም በማጽደቅ ነበር።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በዚኹ ወር ላይ ባካሄደው ኹለተኛ ልዩ ስብሰባው፣ ኹለት የብድር ስምምነቶችን አጽድቋል፡፡ ምክር ቤቱ **በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአለም አቀፍ የልማት ማኅበር** መካከል ለኹለተኛው ዘላቂ እና ኹሉ ዓቀፍ የኢኮኖሚ ልማት ፖሊሲ ማስፈጸሚያ የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ በቀረበ ረቂቅ ዐዋጅ ላይ የተወያየ ሲሆን፣ የብድሩን አስፈላጊነት እና አላማም፣ የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታዋ የተከበሩ መሰረት ኃይሌ  አቅርበዋል፡፡ በብድር የተገኘው ገንዘብ መንግሥት የጀመራቸውን የማሻሻያ ሥራዎች ለመደገፍ እንዲቻል እና የፌደራል መንግሥትን የ2018 ዓ.ም በጀት በቀጥታ ለመደገፍ እንደሚውል ያነሱት መሰረት፣ ብድሩም ከወለድ ነጻ እና በረጅም ዓመታት የሚከፈል መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል፡፡ ምክር ቤትም በብድር ስምምነቱ ላይ ተወያይቶ ስምምነቱን በሙሉ ድምጽ አጽድቆታል፡፡

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዬች ምክር ቤቱ በኹለተኘነት ያፀደቀው የብድር ስምምነት፣ **በኢትዮጵያ መንግስት እና በዚኹ የዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር** መካከል፣ ለፍጥነት መንገድ ልማት ድጋፍ ፕሮጀክት (ሞጆ-ሀዋሳ መንገድ) ማስፈጸሚያ የተደረገውን የብድር ስምምነት ነበር። በብድር የተገኘው ገንዘብ ሊጠናቀቅ የተቃረበውን የሞጆ-ሀዋሳ የፍጥነት መንገድ ሦስተኛ ክፍል ሙሉ ለሙሉ ለማጠናቀቅ እንደሚረዳ የጠቀሱትም መሰረት ኃይሌ ሲሆኑ፣ በብድሩ እየተከናወኑ ያሉ የተለያዩ ሥራዎች ያለችግር እንዲጠናቀቁ የሚያስችል መሆኑን አክለው ተናግረዋል ተብሏል። በመጨረሻም ምክር ቤቱ፣ በብድር ስምምነቱ ላይ ተወያይቶ ስምምነቱን በሙሉ ድምጽ ማፅደቁን የምክር ቤቱ መረጃ ያመለክታል።

# ሹመት

በዚኽች የብሪጅ ሦስተኛ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ሰኔ ወር ውስጥ፣ እንደራሴዎቹ የፈፀሙት ሌላይኛው ሕገ-መንግሥታዊ ተግባር፣ ሹመት መስጠት ነበር።

ሹመቱ የተሰጠው **ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ** ሲሆን፣ ምክር ቤቱም ተስፋዬ ንዋይን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምክትል ሰብሳቢ አድርጎ ሾሟል። እንደ ምክር ቤቱ መረጃ ከሆነም፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አህመድ የቀረበውን የዕጩዎች ሹመት ውሳኔ ሐሳብ ያቀረቡት፣ በምክር ቤቱ የመንግሰት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ ሲሆኑ፣ የምርጫ ሂደቱ ብዝሓነትን ያማከለ እና የማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆኑ መሆናቸውን አብራርተዋል ተብሏል። ከተስፋዬ ንዋይ በተጨማሪም ምክር ቤቱ፣ ተክሊት ይመስል እና ነሲም አሊን የቦርዱ አመራሮች እንዲሆኑ መሾሙን ዘገባው ያሳያል። ተሿሚዎቹም በምክር ቤቱ ፊት ቀርበው ቃለ-መሃላ የፈጸሙ ሲሆን፣ ምክር ቤቱም ሹመቱን በኹለት ድምጸ ተዐቅቦ በአብላጫ ድምጽ አጽድቆታል።

# የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታ

**በዐዋጅ ቁጥር 1390/2017 ዙሪያ**

የኢትዮጵያ እንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በወርኃ ሰኔ ካፀደቃቸው ዐዋጆች መካከል ግዝፈት ያለው ዐዋጅ፣ ለቀጣዩ ዓመት ይሆናል የተባለውን በጀት ማፅደቁ ነበር። ይኽ ዐዋጅ፣ ለ2018 ዓ.ም. በጀት ዓመት አንድ ነጥብ ዘጠና ሦስት ትሪሊዮን ብር ማፅደቅ ሲሆን፣ በዚኹ በጀት ዙሪያ የሚመለከታቸው ባለሥልጣናት እና የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ሰፋ ያሉ ውይይቶችን አድርጎ፣ ዐዋጅ ቁጥር 1390/2017 ሲል በሙሉ አፅድቆታል።

## ምን ተባለ?

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በ42ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ የ2018 የፌዴራል መንግስት በጀት 1 ነጥብ 93 ትሪሊዮን ብር አድርጎ በሙሉ ድምጽ አፅድቋል፡፡ በምክር ቤቱ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄም፣ የ 2018ቱን ረቂቅ በጀት ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳብ አቅርበው ነበር። የዐብይ ኢኮኖሚ ግብን ለማሳካት በጀትን በቁጠባ እና በውጤታማነት ለመጠቀም ታስቦ የተዘጋጀ ረቂቅ በጀት መሆኑን የተናገሩት ደሳለኝ፣ ከጠቅላላ በጀቱ ውስጥ፣ መደበኛ ወጪው 1.2 ትሪሊዮን ብር ሲሆን፣ ለካፒታል ደግሞ 415.2 ቢሊዮን ብር የተበጀተ መሆኑን ለምክር ቤቱ አስረድተዋል፡፡ ከዚኽ ባለፈም፣ ይኽ በጀት ከባለፈው ዓመቱ በጀት ጋር ሲነፃፀር የ34.4 መቶ ዕድገት ማሳየቱን ያነሱት ሰብሳቢው፣ የበጀቱን ወጪ አሸፋፈንም በዝርዝር ለእንደራሴዎቹ አስረድተዋል። ከዚኽ አኳያም፣ የአገር ውስጥ ገቢ 1.1 ትሪሊዮን ብር፣ ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች 129 ቢሊየን ብር እና ከልማት አጋር ድርጅቶች 236 ቢሊዮን ብር፣ እንዲሁም ከልማት ዕቅዶች እርዳታ 47 ቢሊዮን ብር ለማግኘት እንደታቀደ እና የአገር ውስጥ የውጭ ዕርዳታ ገቢ 81 በመቶውን እንደሚሸፍን ደሳለኝ ወዳጄ አብራርተዋል፡፡

ረቂቅ በጀቱን በተመለከተ የበጀት መግለጫውን ለእንደርሴዎቹ ያቀረቡት የገንዘብ ሚኒስትሩ የተከበሩ አህመድ ሽዴ፣ በጀቱ የተጀመሩ የልማት ሥራዎችን ለማስቀጠል፣ ማኅበራዊ ወጪዎችን ለመሸፈን፣ የዕዳ ስረዛን ወደ መካከለኛ ደረጃ ለማውረድ እና ዐብይ ኢኮኖሚውን ማረጋጋት ላይ ያተኮረ እንደሚሆን አብራርተዋል። እንዲሁም፣ የመንግስትን የገቢ አሰባሰብ ለማሳደግ፣ የክልል መንግስታት ገቢን ለማሳደግ እና የታክስ አስተዳደርን ለማጠናከር በልዩ ትኩረት እንደሚሰራ አክለው የተናገሩት ሚኒስትር አሕመድ ሽዴ፣ በጀቱ የ10 ዓመቱን መሪ የልማት እቅድን እና የተሟላ ዐብይ ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያን ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንደተዘጋጀ ጨምረው ማብራራታቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። ከዚኽ ባለፈም፣ በካፒታል በጀቱ መንገዶችን እና ትምህርትን ለማስፋፋት፣ መስኖ እና የግብርና ሥራዎችን ለማዘመን፣ የገጠር እና ከተማ ምግብ ዋስትና እና ልማታዊ ሴፍቲኔትን ለማረጋገጥ እንደሚውል ይውላል ያሉት ሚኒስትሩ፣ በጀቱ የጤናውን ዘርፍ ለማስፋት፣ በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸውን አካባቢዎች መልሶ ለመቋቋም፣ ለመንግስት ቢሮ ግንባታ እና ለንጹሕ መጠጥ ውኃም እንደሚውል አስረድተዋል።



የኢፌዲሪ የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር የተከበሩ አህመድ ሽዴ

በ2018 በጀት ዓመት የ8 ነጥብ 9 በመቶ የኢኮኖሚ እድገት እንደሚመዘገብ መተንበይ መቻሉን ሲናገሩ የተደመጡት ሚኒስትር አሕመድ፣ የአገር ውስጥ ገቢን በማሳደግ እና በማጠናከር ጤናማ የፋይናንስ ሥርዓትን በመፍጠር ዘላቂ የልማት ግቦችን ለማከናወን እቅድ መያዙንም ለእንደራሴዎቹ ነግረዋቸዋል። አሁን ላይ በኢኮኖሚ ማሻሻያው ምክንያት በመንግስት ላይ የተፈጠረው የወጪ ጫና በታሪክ ትልቁ እንደሆነም ያነሱት የገንዘብ ሚኒስትሩ፣ በ2018 በጀት ዓመት የገቢ ምንጩን ለማሳደግ ይሰራል ብለዋል።

በዚኹ በጀት ዙሪያ የመሥሪያ ቤታቸውን መዘርዝር ለማቅረብ ወደ እንደራሴዎቹ ምክር ቤት ብቅ ያሉት የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታው ዶ.ር. ኢዮብ ተካልኝ በበኩላቸው፣ የ2018 ዓ.ም. በጀት በዋናነት በአገር ውስጥ ገቢ ሲበጀት፣ ቀሪው ከውጭ የልማት አጋሮች በሚገኝ ድጋፍ እና ወለድ የማይከፈልባቸው የችሮታ ጊዜ ያላቸውን የብድር አቅርቦቶች ብቻ ማዕከል በማድረግ የበጀት ጉድለቱን ለማሟላት መንግስት ስልት መንደፉን ለምክር ቤቱ አባላት አስረድተዋል። በጀቱ የአየር ንብረት ለውጥን፣ የአካል ጉዳተኞችን በተለይም የሴቶች እና ሕፃናት ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ መታቀዱን የተናገሩት ሚኒስትር ዴኤታው፣ በጀቱ ሲታቀድ ዛሬ ላይ ያለውን ፍላጎት ብቻ በማሟላት የዐብይ ኢኮኖሚውን ወደ ጫና የሚወስድ እንዳይሆን ጤናማ ዕድገትን የሚያረጋግጥ ሂደትን ትኩረት በማድረግ የቀረበ መሆኑን ለእንደራሴዎቹ አብራርተውላቸዋል።

## በጀቱን ዶላሩ ዋጠው ይሆን?

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በጀቱን አስመልክቶ ባወጣው አጭር መግለጫ፣ በበጀቱ ቅድምና የሚወስዱትን ርዕሰ-ጉዳዮች ጠቅሶ ነበር። እንደ ምክር ቤቱ መግለጫ፣ ይኽ የቀታዩ ዓመት በጀት የአገር ደህንነትን ማስጠበቅ፣ ምርት እና ምርታማነትን ማሳደግ እንዲሁም በተፈጥሮ እና በሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት የተፈናቀሉ ዜጎችን ከመርዳት አንጻር የተዘጋጀ ነው ተብሏል።

ከዚኽ በተጨማሪ በጀቱ ከ2018 እስከ 2022 ዓ.ም. ድረስ ያለውን የመካከለኛ ዘመን የዐብይ ኢኮኖሚ እና ፊስካል ማዕቀፍን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ እንደሆነ መግለጫው ጠቁሟል። የዐብይ ኢኮኖሚ እና ፊስካል ማዕቀፉ የመንግስትን ገቢ መሰረት በማስፋት ወጪን ለመሸፈን እንዲያስችል ሆኖ መዘጋጀቱም ተጠቅሶ ነበር። በኢትዮጵያ የተረጋጋ የዐብይ ኢኮኖሚን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት የሚደግፍ ሆኖ የተዘጋጀ ነው የተባለለት ይህ ማዕቀፍ፣ ከመንግስት ገቢ አሰባሰብ እና ሀብት አመዳደብ አኳያ ያሉ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን የሚያመላክት እንደሆነም ተገልጿል። ይኽ የአንድ ነጥብ ዘጠና ሦስት ትሪሊዮን ብር በጀት፣ በዘንድሮው ዓመት በመደበኛነት እና በተጨማሪነት ከጸደቀው የበጀት መጠን ጋር ሲነጻጸር በ29 በመቶ ገደማ ዕድገት አሳይቷል። የ2018 በጀት ከዘንድሮው ጋር ሲነጻጸር በ500 ቢሊዮን ብር ገደማ ጭማሪ ቢኖረውም በዶላር ግን ከፍተኛ ቅናሽ ማሳየቱን ብሪፉ ተረድታለች።

በግንቦት 2016 ዓ.ም የጸደቀው የዘንድሮው 971.2 ቢሊዮን ብር መደበኛ በጀት፣ በወቅቱ ምንዛሬ 17 ቢሊዮን ዶላር ገደማ ነበር፤ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በኅዳር 2017 ዓ.ም. ያጸደቀው 581.98 ቢሊዮን ብር ተጨማሪ በጀት ደግሞ በዚያን ጊዜ በነበረው የዶላር ምንዛሬ ሲሰላ 4.8 ቢሊዮን ዶላር ሆኗል። የኹለቱ ድምር የ2017ን አጠቃላይ በጀት ከ1.5 ትሪሊዮን ብር በላይ ወይም 22 ቢሊዮን ዶላር ገደማ አድርሶታል። የ2018ቱ በጀት የዶላር ምጣኔ ደግሞ፣ ዐዋጁ በፀደቀበት ዕለት በነበረው፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አማካይ ዕለታዊ የምንዛሬ ጠቋሚ የዶላር ምንዛሬ ስንመለከተው፣ ዐሥራ አምስት ነጥብ አራት ቢሊየን ዶላር ሆኗል። ከዚኽ አኳያም፣ የ2017ቱ በጀት፣ በወርኃ ሰኔ ከፀደቀው የ2018 በጀት ጋር ሲነጻጸር፣ ወደስድስት ቢሊዮን ዶላር ገደማ ልዩነት ያሳያል፤ አልያም በዶላር ምጣኔ ካየነው ወደ ሠላሳ ስድስት በመቶ ያሃል ቅናሽ ያሳየ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ይኽን በጀት አስመልክቶ፣ የገንዘብ ሚኒስቴር ዝርዝር የበጀቱ መግለጫ፣ በጀቱን መሸፈኛ ምንጮችን በዝርዝር አቅርቧል። የበጀቱ ምጣኔ በዶላር ሲሰላ ከቀደመው ዓመት ማነሱ፣ አገሪቷ ያሉባትን ብድሮች ለመክፈልም ሆነ ወደ አገር ቤት የሚገቡ ምርቶችን ለመግዛት የሚገጥሟትን ተግዳሮቶች ከፍ እንደሚያደረገው መገመት ቢቻልም፣ ከይፋዊ አበደሪዎቿ በኩል የዕዳ አከፋፋል ሽግሽግ እንደሚደረግ መነገሩ ደግሞ፣ ተግዳሮቱን የሚያቀል ይመስላል።

ከዚኽ አንፃርም፣ የኢትዮጵያ መንግስት ከአበዳሪዎቹ አገራት እና ተቋማት ጋር ሲያካሂደው የነበረው የዕዳ ሽግሽግ ድርድር መጠናቀቁን የገንዘብ ሚኒስትሩ አህመድ ሽዴ በጀቱ በፀደቀ ማግስት ማስታወቃቸው አይዘነጋም። ድርድሩ የተጠናቀቀ በመሆኑ በቅርቡ ይፈረማል ያሉት ሚኒስትሩ፣ በዚኽም ኢትዮጵያ ከአበዳሪ አገራት የወሰደችውን የ3.5 ቢሊዮን ዶላር ዕዳ ለመክፈል እፎይታ እንደምታገኝ ተናግረዋል። ባለፉት ሦስት ዓመታት በዕዳ ሽግሽግ ከፍተኛ ጥቅም አግኝተናል ያሉት ሚኒስትሩ፣ በቀጣይም ባለፉት 15 ዓመታት ስንበደር ለቆየነው ገንዘብ የክፍያ ጊዜ እፎይታ እናገኛለን ማለታቸውን የሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸው መረጃ ያሳያል። ምሚንስትር አሕመድ አክለውም፣ ከአበዳሪዎች ጋር በተግባባንበት እና በተራዘመው የክፍያ ሰሌዳ መሰረት፣ ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ ዕዳውን መክፈል እንቀጥላለን ሲሉ መናገራቸውንም መረጃው ጠቅሷቸዋል። ከዚኽ የዕዳ እፎይታ ድርድር ባለፈም፣ ይኸው በጀት በፀደቀ ሰሞን እንደተሰማው፣ የኢትዮጵያ መንግሥት እና የዓለም ባንክ የአንድ ቢሊየን ዶላር የፋይናንስ ስምምነት ፈርመዋል። እንደ ብሪፉ ዕምነትም፣ ይኽ በስምምነቱ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን የጠቀስነውን ተግዳሮት በማለሳለስ የተወሰነ አስተዋጽዖ እንደሚኖረው እንገነዘባለን።

## "የሞት ሽረት ጉዳይ ነው"

እንደ ብሪፉ አጠር ያለ ዳሰሳ ከሆነ፣ የኢትዮጵያ መንግስት፣ ቀጣዩን ወደ ኹለት ትሪሊዮን ብር የሚጠጋውን በጀት ገቢ አብዝቶ ለመሰብሰብ ያቀደው ከአገር ውስጥ ነባር እና አዳዲስ የግብር ዓይነቶች መሆኑ፣ ቀጣዩን በጀት በከፊልም ቢሆን የተለየ ያደርገዋል። በዚኹ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ የተናገሩት የገንዘብ ሚኒስትሩ አሕመድ ሽዴም፣ የፌደራል መንግስት የበጀት ጉድለቱን ለመሙላት አገር ውስጥ ካለ የገንዘብ እንቅስቃሴ በፋይናንስ ተቋማት አማካኝነት እንደሚበደር አብራርተዋል። ስንበደር በአዲሱ የገንዘብ ፖሊሲ ነው ስለምንበደር ከበፊቱ ወደድ ያለ ነው የሚሆነው ያሉት አሕመድ፣ ስለዚህ መንግስት እንደ ከዚህ በፊቱ በቀላሉ ከኢኮኖሚው ውስጥ የሚበደርበት ኹኔታ አብቅቷል ሲሉም በአጽንኦት ሲናገሩ ተደምጠዋል። ነገሩን ሲያብራሩም፣ አዲስ የልማት ጥያቄ ለመፍታት ብለን ከብሔራዊ ባንክ የምንበደርበት ሁኔታ አብቅቶለታል ያሉት ሚኒስትሩ፣ አዲስ የልማት ጥያቄ ለመፍታት ብለን በቀላል የወለድ ምጣኔ ከኢኮኖሚው ውስጥ የምንበደርበት ሁኔታም አብቅቶለታል ሲሉ ደጋግመው ተናግረዋል። ይኽ የመግለጫቸው አካሄድም አዲስ የገንዘብ ፖሊሲ እንደሆነ የተናገሩት አሕመድ፣ አዲስ ፊሲካል ፖሊሲ የሚባለው ይሄ ነው ሲሉም በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በነበራቸው ውሎ መጠቆማቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ያሳያል።

የኢትዮጵያ ዐብይ ኢኮኖሚ የተረጋጋ የሚሆነው እና እድገት የሚቀጥለው፣ ገቢን በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ እንደሆነ የገለጹት ሚኒስትሩ፤ ይኽ ጉዳይ ለፌደራል መንግስቱ የሞት የሽረት ጉዳይ ነው ጠበቅ አድርገው ሲናገሩ ተሰምተዋል። መንግስት የሚሰበስበው ታክስ ከአጠቃላይ አገራዊ ምርት ጋር ያለው ጥመርታ ከብዙ አገራት ጋር ሲነጻጸር አሁንም ዝቅተኛ” መሆኑን ያነሱት የገንዘብ ሚኒስትሩ፣ መንግስት በሚቀጥሉት አራት ዓመታት ይሄንን በአራት በመቶ የማሳደግ እቅድ እንዳለውም አመልክተዋል። በእርሳቸው መሥሪያ ቤት የተዘጋጀው የበጀት ዕቅዱ ሰነድም፣ የቀጣዩ ዓመት ታክስ ከአጠቃላይ አገራዊ ምርት ጋር ያለው ጥመርታ፣ ዘንድሮ ካለው በ1.2 በመቶ ጭማሪ ያስመዘግባል ተብሎ እንደሚጠበቅ አስፍሯል። በታክስ ላይ የተጣለውን እቅድ ለማሳካት በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ የሚመራው የዐብይ ኢኮኖሚ ኮሚቴ እንዲሁም ለዚሁ ዓላማ የተቋቋመው ግብረ ኃይል ዝርዝር ውይይት ማድረጋቸውን ጨምረው የገለጹት አሕመድ ሽዴ፣ በዘንድሮ በጀት ዓመት የተመዘገበው የታክስ አሰባሰብ አፈጻጸም በቀጣዩ ዓመትም ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ የሚመጣውን ዘመን ከበድ ያለ ሥራ ጠቆም አድርገዋል።

ይኽንን የገንዘብ ሚኒስትሩን ጠበቅ ያለ ዕቅድ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ልንመለከተው ስንሞክር የምናገኘው ስዕል ጥቂት ዕይታዎችን ያቀብለናል። መንግስት በዘንድሮው በጀት ዓመት ከታክስ እና ቀረጥ ለመሰብሰብ አቅዶ የነበረው የገንዘብ መጠን 900.2 ቢሊዮን ብር ነበር። በበጀት ዓመቱ 11 ወራት ውስጥ የተሰበሰበው ገቢ 815.3 ቢሊዮን ብር እንደሆነ የገቢዎች ሚኒስቴር ማስታወቁ አይዘነጋም (ለዚኽ መረጃ ይኽንኑ የእንደራሴዎች ዕትም የተቋማት ሪፖርት ንዑስ ክፍል ይመለከቷል)። የገቢዎች ሚኒስትሯ አይናለም ንጉሴ ለእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ባቀረቡት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት፣ ከአገር ውስጥ ገቢ ባለፉት 11 ወራት ለመሰብሰብ የተቻለው 436.48 ቢሊዮን ብር እንደሆነ ገልፀው ነበር። ይኽ ገቢ የእቅዱን 96.79 በመቶ ያሳካ እንደሆነ የገለጹት ሚኒስትሯ፣ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ ጋር ሲነጻጸር ደግሞ 48 በመቶ እድገት ያለው መሆኑን ተናግረው ነበር። ይኽንን የአይናዓለምን ሪፖርት ያደመጡት እንደራሴዎቹም፣ የገቢ መጠኑ ከባለፈው አመት ከፍ ይበል እንጂ፣ ወደ ዶላር ተቀይሮ ቢነጻጸር የእዚህ ዓመቱ ገቢ መጠን ያነሰ ነው ሲሉ ትችታቸውን ማቅረባቸው አይዘነጋም። ይኽን ማንፀሪያ ስናደርግም፣ በቀጣዩ ዓመት ይሰበሰባል የተባለው ከአንድ ትሪሊየን ብር በላይ የሆነ የታክስ ገቢ፣ ከዚኽኛው ዓመት ከተሰበሰበው እና በሙሉ በጀት ዓመቱም ይሰበሰባል ከተባለው ገቢ በዶላር ምንዛሬ የማነሱ ነገር አይቀሬ ይመስላል።

በገንዘብ ሚኒስትሩ አሕመድ ሽዴ የተጠቀሰው አዲስ የገንዘብ ፖሊሲ፣ አዳዲስ የታክስ መሠረቶችን ማስተዋወቅ ላይ እና በነባሮቹ የታክስ ዓይነቶች ላይም የታክስ ምጣኔን መጨመርን ያለመ መሆኑን ብሪጅ ተገንዝባለች። ለማሳያ ያህልም፣ ከቀደመው ዓመት አንስቶ፣ ከዚኽ ቀደም በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ውስጥ ያልተካተቱ አገልግሎቶች ተጨማሪ ዕሴ ታክስ እንዲጣልባቸው የገንዘብ ሚኒስቴር መወሰኑ ያተወሳል።

የመኖሪያ ቤቶች የኤሌትሪክ አገልግሎት እና የንጹሕ መጠጥ ውኃን መሰል ሕዝባዊ ግልጋሎቶች ወደ ተጨማሪ ዕሴት ታክስ ውስጥ የተካተቱ መሆናቸውን በማስሳያነት መጠቀስ ይቻላል። ከዚኽ በተጨማሪም፣ በቴሌኮሚኒኬሽን እና ድንበር ዘለል የዲጂታል አገልግሎቶች ላይም ኤክሳይስ ታክስ ሲጣል፣ የከተማ አስተዳደሮችም የንብረት ግብርን እንዲሰበስቡ ባቀደመው ጥር ወር ላይ እንደተፈቀደላቸው ይታወሳል። እነዚኽን የታክስ ዓይነቶች አካተን፣ የአገሪቷን የታክስ ስብሰባ ምጣኔ ስንመለከት፣ በእርግጥም የገንዘብ ሚኒስትሩ እንዳሉት፣ ከአጠቃላይ አገራዊ ምርት አኳያ ኢትዮጵያ የምትሰበስበው ግብር ያለው ምጣኔ ከሰሃራ በታች ካሉት አገራት ጭምር ዝቅተኛው መሆኑን መረዳት ይቻላል። ነሐሴ 9 2017 ዓ.ም. የወጣው እና በገንዘብ ሚኒስቴር እና አጋር የምርምር ተቋማት የተሰራው “Ethiopia’s Tax-to-GDP Ratio: Benchmark Estimation and Performance Analysis” የተሰኘው ጥናትም፣ ይኽንኑ ሃቅ በቁጥሮች አስደግፎ አቅርቧል። ሪፖርቱ የኢትዮጵያ 15 በመቶ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምጣኔ መሆኑን፣ ኬንያ 16 በመቶ፣ ሩዋንዳ 18 በመቶ፣ ኡጋንዳ 18 በመቶ እንደሆነ ገልጾ፣ ከሰሃራ በታች ያሉ አገሮች አማካይ ምጣኔ ደግሞ 17.5 በመቶ መሆኑን አመላክቷል:: የጥናት ቡድኑ በኢትዮጵያ አሁን በሥራ ላይ ያለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ምጣኔን፣ ከሰሃራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ አገሮች ወደ ደረሱበት አማካይ ምጣኔ 17.5 ከፍ  እንዲል ምክረ ሐሳብ ቢያቀርብም፣ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ ምጣኔው ባለበት 15 በመቶ ላይ እንዲቀጥል መወሰኑን ብሪጅ እጅጉን በአዎንታዊ እርምጃነት ትመለከተዋለች።

ብሪጅ፣ በገንዘብ ሚኒስትሩ አሕመድ ሽዴ፣ የሞት እና የሽረት ተብሎ የተጠራው የቀጣዩን ዓመት የበጀት ምንጭ በዋናነት ከአገር ቤት y የሚሰበስበው ዕቅድ፣ በዜጎች ላይ በተለይም ቋሚ ገቢ በሚያገኙት የታችኛው የኢኮኖሚ መደብ ላይ ጫና እንዳይፈጥር ትስጋለች። በእርግጥ ይኽ ስጋት የብሪጅም ሆነ የሌሎች የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ብቻም ሳይሆን፣ ዓመት የሞላውን የኢትዮጵያ ዐብይ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በብዙ ሚሊየን ዶላሮች እየደገፈ ያለው ዓለም ዓቀፉ የገንዘብ ተቋም (አይኤም ኤፍ)ም ነው። ተቋሙ ከጥቂት ግዜያት በፊት ባወጣው ሪፖርት፣ በኢትዮጵያ ያለው የግብር ሥርዓት፣ በተለይም በዝቅተኛ ገቢ ላይ ባሉ ግብር ከፋዮች ላይ የሚጣለው ከፍተኛ የግብር ተመን፣ ዜጎች ወደ መደበኛ የሥራ ዘርፍ እንዳይገቡ ተስፋ እያስቆረጣቸው መሆኑን ያመለከተ ነበር። እንደ ዓለም ዓቀፉ የገንዘብ ተቋም ከሆነ፣ የኢትዮጵያ የግብር ሥርዓት አወቃቀር በዝቅተኛ የገቢ ደረጃ ላይ ባሉ ዜጎች ላይ ከፍተኛ የግብር ተመን የሚጥል ሲሆን፣ ይህም ድርጅቶች እና ሠራተኞች መደበኛ ባልሆነው የንግድ መስክ ውስጥ እንዲቆዩ ሊያደርግ ይችላል ይላል። ይህ ደግሞ ለልማት የሚውለውን የግብር ገቢ እንዲቀንስ ያደርጋል ሲልም ስጋቱን መግለጡ አይዘነጋም።

## የብሪጅ ምክረ ሐሳብ

- የ2018ቱ በጀት በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በፀደቀበት ዕለት፣ ከተወሰኑ እንደራሴዎች በኩል አንድ አስተያየት ሲሰጥ ተስተውሏል። ይኸም፣ የበጀት ድልድሉ በተለይም ለክልሎች የተመደበው የድጎማ በጀት ፍትሓዊነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የሕዝብ እና የቤት ቆጠራ መደረግ እንዳለበት መነሳቱን ብሪጅ አስተውላለች። ከዚኽ አኳያም፣ በእርግጥም የሕዝብ እና የቤት ቆጠራ ቢካሄድ፣ ቆጠራው በአጠቃላይ ለአገራዊ ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች ከሚሰጠው ምትክ አልባ ጠቀሜታ ባለፈ፣ እንደራሴዎቹ እንዳሉትም በተለይም ከልሎቹ በተመደበው በጀት ዙሪያ ሊሞር የሚችልን ቅሬታ በቅጡ ያስወግዳልና፣ የፌደራል መንግሥቱ በሚችለው አቅም እና ጊዜ ቆጠራውን ቢያካሂድ ፋይዳው የጎላ ነውና ቢታሰብበት ስትል ብሪጅ ምክረ ሐሳቧን ታቀርባለች፤ ምናልባትም፣ የቆጠራውን ውጤት ተከትሎ ሊመጡ የሚችሉ የክልል ድጎማ ተኮር ቅሬታዎች ቢኖሩ እንኳን፣ በተጨማሪ በጀት ቅሬታዎቹን መቅረፍ ይቻላል ብለን እናምናለን።

- የኑሮ ውድነቱ በተለይም በመንግስት ሠራተኛው ላይ ያመጣውን ጫና ለመቅረፍ፣ መንግስት የሠራተኛውን መነሻ የደመወዝ ወለል ከቀጣዩ መስከረም ወር ጀምሮ ከፍ ሊያደርግ መወሰኑን ብሪጅ በአዎንታዊ እርምጃነት ትመለከተዋለች። ከዚኽ ባለፈ ግን፣ በተለይም በታችኛው እርከን ያለውን የማኅበረሰብ ክፍል ገቢ እየበላ ያለው የዋጋ ግሽበቱ መሆኑ ይታወቃል፤ እናም መንግሥት የዋጋ ግሽበቱን ለማርገብ ከሚወስዳቸው የተለያዩ የገንዘብ እና ፊስካል ፖሊሲዎች ባለፈ፣ ሰው ሰራሽ የዋጋ ንረቱን ከዚኽ በላይ ቢቆጣጠር ነገሮች የተሻሉ እንደሚሆኑ ይታወቃል፤ እናም፣ በተለይም በዚኽ ሰው ሰራሽ የዋጋ ግሽበት ላይ የተሰማሩ የንግድ ተቋማት ላይ ጠንከር ያለ ቁጥጥር ያደርግ ዘንድ ብሪጅ ምክረ-ሐሳቧን ማቅረብ ትሻለች።

- የወጪ ንግዱ ዋና የውጭ ምንዛሬ ምንጮች እየሆኑ የመጡት ቡና እና ወርቅ እንደመሆናቸው፣ እነዚህ ምርቶች ደግሞ በብዛት አሚገኙት አሁን በከፊል ግጭት ውስጥ ባሉት ክልሎች መሆኑ፣ ግጭቶችን መንግስት በሚችለው ፍጥነት፣ ትግስት እና ሆደ ሰፊነት የሚፈቱበትን መላ አብዝቶ ቢያስሳቸው፣ ሰላም ከማስፈን ባለፈ፣ የአገራችን የንግድ ሚዛን ሊስተካከል ብቻም ሳይሆን ለ2018 በጀት ዓመት የተያዘው ዕቅድም ይሳካልና፣ የፌደራል መንግሥቱ በያዘው ሰላም አምጪ መንገድ እንዲገፋበት ብሪጅ የዜግነት ምክሯን ማስተላለፍ ትፈልጋለች።

- በጀቱ በረቂቅ ደረጃ ለውይይት ቀርቦ ሳለ፣ እንደራሴዎቹ ካነሷቸው ነጥቦች መካከል አንደኛው፣ ለአገሪቷ የዲሞክራሲ ተቋማት የሚመደብላቸው በጀት አነስተኛ መሆን፣ ሥራቸውን በአግባቡ እንዳይሰሩ እግዳት ሆኖባቸዋል የሚለው ነው። ከተጠናቀቀው በጀት ዓመት አኳያ፣ ይህን ችግር ማስታዋኣልም ይቻላልና፣ ብሪጅም ይኽ የእንደራሴዎቹ አስተያይት፣ በቀጣይ ሊኖር በሚችል የበጀት ማስተካከያ ላይ አትኩሮት ቢሰጠው፣ ለዲሞክራሲ ግንባታው ፋይዳው የጎላ መሆኑን በማስታወስ፣ የእንደራሴዎቹን አስተያይት የሚመለከታቸው ተቋማት አትኩሮት ይስጡበት ማለት እንሻለን።

- ይኽ በጀት፣ ከላይ ለማንሳት እንደሞከርነው ብዙዉ ክፍሉ በአገር ቤት ምንጮች እንደሚማላ ከመጠበቁ አንፃር፣ በጀቱን እጅጉን በጥንቃቄ ሥራ ላይ ማዋል እንደሚያስፈልግ ማስታወስ አያስፈልግ ይሆናል፤ ነገር ግን፣ በቀደመው ዓመት፣ የፌደራል ኦዲት መሥሪያ ቤቱን ጨምሮ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ሪፖርቶቻቸውን ካቀረቡ የተለያዩ ተቋማት እንደተገነዘብነው፣ በጀትን በቁጠባ መጠቀም ለአሁኒቷ ኢትዮጵያ እጅጉን አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ስለሆነም፣ ተቋማት የሚከውኑትን የትኞቹንም ግዢዎች በኤሊክትሮኒክ ግዢ እንዲፈፅሙ የበረታ ቁጥጥር ቢደረግ፣ የበጀት መባከኖችን መቀነስ ይቻላልና ይኽ ጉዳይ ልዩ አትኩሮት ቢሰጠው ስንል ምክረ-ሐሳባችንን ማቅረብ እንፈልጋለን።

- ሌላይኛው የብሪጅ የምክር ሐሳብ ነጥብ፣ በአዲሱ በጀት ክልሎች ራሳቸውን ወደ መቻል እንዲሄዱ የሚያደርግ አዝማሚያ በመከተሉ ዙሪያ ነው። የገንዘብ ሚኒስትሩ አሕመድ ሽዴ በበጀቱ ውይይት ወቅት እንዳሉት፣ ለክልሎች የሚሰጠው ድጎማ እያደገ ቢሄድም፣ በቀጣይ ግን ክልሎች የራሳቸውን አቅም በማጎልበት ገቢያቸውን የሚሳድጉበት እና በራሳቸው አቅም መዋዕለ ንዋይ የሚስቡበትን መንገድ መተለም ይኖርባቸዋል። ከዚኽ በተጨማሪ፣ ክልሎች እስከ 70 በመቶ የሚሆነውን ለሰብዓዊ ዕርዳታ የሚወጣውን ወጪ በራሳቸው ወደ መሸፈን እንዲሄዱ አቅጣጫ መያዙም ተሰምቷል። ተጨባጭ የሆኑትን ነገሮች ስንመለከት ግን፣ በተለይም እንደ አማራ፣ ትግራይ፣ ኦሮሚያ እና አፋር ያሉት በቀደመው የሰሜኑ ጦርነት ወቅት ሰፊ ሰብዓዊ እና ቁሳዊ ጉዳቶችን ያስተናገዱት ክልሎች (ለእነዚኽ ክልሎች መልሶ ግንባታ የሚያስፈልገው ገንዘብ ወደ 20 ቢሊየን ዶላር መሆኑ ይታወሳል) ይኽን አቅጣጫ ለመከተል እጅጉን አቅም እንደሚያጣራቸው ብሪጅ ትገነዘባለች። ስለዚህም፣ የፌደራል መንግሥቱ በእርግጥም አኹን የያዘው፣ ፊስካል ተኮር ኃላፊነቶችን ኢ-ማዕከላዊ ማደረጉ-የፊስካል ፌደራሊዝሙን በእግሩ ለማቆም ይበል የሚያሰኝ እርምጃ ቢሆንም ቅሉ፣ የጠቀስናቸው በጦርነቱ የተጎዱ የፌደራሉን መንግሥት ድጋፍ የሚሹት ክልሎችም ሆኑ፣ ፌዴሬሽኑን የተቀላቀሉት አዳዲሶቹ ክልሎች፣ ይኽን አቅጣጫ ቢያንስ በቀጣዩ በጀት ዓመት ለመተግበር እጅጉን አቅም ይጎድላቸዋልና፣ ነገሩን መንግሥት አቅማቸው በሚጎለብትበት አቅጣጫ በኩል ቢተገብረው በጎ ውጤት ይኖረዋል ስትል ብሪጅ ምክረ-ሐሳቧን ማቀበል ትሻለች።

[1]ፋና ሚዲያ ኮርፖሬሽን (2017 ነሐሴ 13). የተጨማሪ እሴት ታክስ ምጣኔ 15 በመቶ ሆኖ እንዲቀጥል ተወስኗል – የገንዘብ ሚኒስቴር። ከhttps://www.fanamc.com/archives/299209 የተወሰደ።

[2]International Monetary Fund. African Dept. (2025). The Federal Democratic Republic of Ethiopia: 2025 Article IV Consultation, Third Review Under the Extended Credit Facility Arrangement, and Financing Assurances Review-Press Release; Staff Report; Staff Supplement; and Statement by the Executive Director for The Federal Democratic Republic of Ethiopia. IMF Staff Country Reports, 2025(188), A001.

- ብሪጅ ከበጀት ዝርዝሩ መረዳት እንደቻለችው፣ የበጀቱ ብዙ ድርሻ መደበኛ ለሚባለው የመንግሥት ወጪ ነው። ለመደበኛ ወጪው የተመደበው የገንዘብ መጠን አንድ ነጥብ ኹለት ትሪሊየ ብር (ከአጠቃላዩ 61 በመቶ) መሆኑ፣ ምናልባትም ያልተስተዋለ አንድ አሉታዊ ገጽ እንዳያመጣ ብሪጅ ትስጋለች። ይኸም፣ መንግሥት ይኽን ያህል የመደበኛ የብር መጠነን ለማሟላት፣ የአገር ውስጥ የብድር ምንጮችን ለመጠቀም እንደመገደዱ፣ ይኽ ሂደትም የአገር ውስጡን የብድር ምንጮች በማሳሳት፣ የግል ክፍለ-ኢኮኖሚው የሚፈልገውን የፋይናንስ ምንጭ እንዳያደርቀው ብሪጅ ስጋቷን መግለጽ ትሻለች። በተለይም፣ መንግሥት ኢኮኖሚው በግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ እንዲመራ አብዝቶ ከመፈለጉ እና በፖሊሲ ጭምር ድጋፍ ለማድረግ እንደመትጋቱ፣ ይኽ ሂደት ያልታሰበ ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮት እንዳይፈጥር በተለይም የገንዘብ ሚኒስቴር የፊስካል እና የሞኒተሪ ፖሊሲዎቹን ነባራዊነትን በተንተራሰ መልኩ ተጨባጭ ሂደቶቹን እየተመለከተ ማስፋት እና መለጠጡ ላይ እትኩሮት እንዲሰጥ ስትል ብሪጅ ምክረ-ሐሳቧን ማቅረብ ትፈልጋለች።

- የመጨረሻው ነጥባችን፣ የኢትዮጵያ ዋንኛ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ ወደ ውጪ የሚላኩት ምርቶች ከመሆናቸው ጋር እና በቅርቡ የፕሬዝደንት ዶናልድ ትራምፕ መንግስት በሌሎች አገራት ላይ እንዳደረገው ኹሉ፣ ኢትዮጵያም ላይ ከጣለው የዐሥር በመቶ ታሪፍ ጋር የተያያዘ ነው። እ.አ.አ. በ2024 ኢትዮጵያ እና አሜሪካ 4.3 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት የንግድ ልውውጥ እንደነበራቸው የዩናይትድ ስቴትስ የንግድ ተወካይ ቢሮ መረጃ ያሳያል። ኢትዮጵያ በቀዳሚነት ወደ አሜሪካ ከምትልካቸው ምርቶቿ መካከል ቡና፣ የቅባት እና የጥራጥሬ እህሎች እንዲሁም ጨርቃ ጨርቅ እና የቆዳ ውጤቶች እንደሚገኙበት ይታወቃል። በተለይም ቡና ብዙዉን ድርሻ ይይዛል። ከዚክ አኳያ ስንመለከተውም፣ ይኽ የፕሬዝደንት ትራምፕ ውሳኔ አገራችንን አይጎዳም ብሎ ማሰብ እጅጉን አስቸጋሪ ነው። እንደ ብሪጅ መረዳት ከሆነም፣ ይኽን ጉዳት ለመቅልበስ፣ መንግስት ሊሂድበት ከመረጠው ሌሎች የውጪ ምርት መዳረሻ አገራትን ከመፈለግ ባለፈ፣ ከአሜሪካ መንግሥት ጋር ንግድ ተኮር ድርድር ቢያደርግ ቢያንስ የታሪፉ ምጣኔ የሚቀነስበትን መፍትሔ ሳይገኝ አይቀርምና፣ የፌደራል መንግሥቱ ድርድሩ ላይ ቢያተኩር ስትል ብሪጅ የመጨረሻ ምክረ-ሐሳቧን ማቅረብ ትሻለች።

እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

**ከራስ ውርድ፦**

“በእነዚኽ ወርኃዊ የእንደራሴዎቹ ጥቅንሮች ውስጥ ያሉት ኹሉም የገጸ-ሰብ እና የገጸ-መስኮች ምስሎች የተገኙት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ይፋዊ የመረጃ ምንጮች ነው፤ እንዲኹም፣ ኹሉም ቁጥራዊ ዘገባዎች የተወሰዱትም ከዚኽ ምንጭ ነው። ዳሰሳዊ ምልከታዎቹ፣ አጠቃሎዎች እና ተያያዥ ትንታኔዎቹ የተቋማችን ናቸው።”

# እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

**BRIDGE** Research & Innovation for Democratic Governance and Enhanced Peace

+251 115 57 74 96

+251 911 86 12 34

research@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.